# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

ወርሃዊ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## የማህበረት ችግር

### ክፍል አንድ

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፥

P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር **3**

ጥር – የካቲት 1965

# መግቢያ

በፓሪስ:አንቶኒ: ተሰበሰበ ለነበረው በአውሮፓ የኢትዮጵ
ያ ተማሪዎች ማህበር 12ኛ ጉባኤ ከአሜሪካ የኢትዮጵያ ተማ
ሪዎች ማኅበር አንድ ጽሁፍ ተልኮ ነበር::የዚህን ጽሁፍ ሁለ
ተኛ ክፍል በዚህ መጽሄት ላይ አውጥተነዋል::በዚህ መልእክት
ውስጥ በአሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በኢትዮጵያ ተ
ማሪዎች እንቅስቃሴ ላይ የመሰላቸውን አስተያየት አቅርበዋል::

ብዙ ነጥቦች ማብራሪያ ይጠይቃሉ::በተለይም የተማሪዎቹ
ን እንቅስቃሴ በቅርብ ላልተከታተለው አንባቢ ችግር መፈጠሩ
አይጠረጠርም::በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች አባል የሆነ በ
ሰሜን አሜሪካ ሲካሄድ የነበረውን ተጠግቶ ያላጠና እንኳን የ
ብዙዎቹን የክርክር ነጥቦች እውነተኛነት በሙሉ ሊያመዛዝንና
ሊፈርድ አይችልም::ለወደፊት ክርክር እንዲጠቅም ለማባበቢያ ያ
ህል የመጽሄቶቻችንን ተግባሮች ባጭሩ ለመዘርዘር ይቻላል::

1ኛ/ የጸረጉልታዊና የጸረኢምፔሪያሊስት አቋም መግለጫ:
ማስፋፊያ:መሟገቻ: የተለያዩ የጸረጉልተኛና የጸረኢምፔሪያሊስት
መደቦች: የህብረተሰብ ክፍሎች አባብ ማቀረቢያ ልሳናችን ናቸው::
ለዚህም ስራ የሆነ ጭምከራቢ አላቸው::

2ኛ/ የአባብም ክርክር በሚደረግበት ጊዜ ውሃ ቀጠነ
በሉ የሌለ ደዌ ለመፈለግ ባይሆን በቀንነት ላይ የተመረኮዘ
ሙግትና ትችት ማድረግ ያስፈልጋል::

3ኛ/ በምንም አይነት የጸረጉልታዊና የጸረኢምፔሪያሊስ
ት ንቅናቄያችንን ለመሰበርና ለመበተን ለሚደረጉ ግልጽ ወይም

ረቂቅ ጥረቶች መባሪያ እንዳይሆኑ እያንዳንዱ አባል በንቃት መ
ጠበቅ ያስፈልገዋል::

4ኛ/ ለክርክሮች ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ ነው:: ያለ
በለዚያ ነፋስ የሚወሰደው ተራ ንግግር ሆኖ ይቀራል::

ት ግ ላ ች ን

## ክ ፍ ል ሁ ለ ት

## በኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ውስጥ ስለተነሳው ችግር፣

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ከኢትዮጵያ ህብረተ ሰብ ውስጥ ተነጥለው ሊታዩ አይቻልም:: በመሃከላቸው ያለውም ግንኙ ነት፣ መለያየትና መተባበር፣ ከመደብ ትግል ውጭ ሊታይ አይቻልም:: በኢትዮጵያ ህብረተ ሰብ ውስጥ ያሉት መሠረ ታዊ ቅራኔዎች በመላው አገር ህዝብና በኢምፔሪያሊዝም መሃ ከል በፊዩዳሊዝምና በሰፊው ህዝብ መሃከል ያሉት ናቸው:: ባልሆነም ከፊዩዳል መደብና ከጥገኛ ቡርዧው መደብ በስተቀር የተቀሩት መደቦችና ህብረሰብ ክፍሎች የሚመጣው ረቮሉሽን ሁሉንም የሚጠቅማቸው እንጂ የማይጎዳቸው ስለሆነ፣ በሁለተኛ ደረጃ በመሃከላቸው የሚገኙትን ቅራኔዎች ለጊዜው በማለፍ (ትግሉን በማዘግየት) የጋራ ጠላቶቻቸውን ለማጥፋት የህብረት ግንባር ሊፈጥሩ ይችላሉ:: ነገር ግን እነዚህ መደቦች የህ ብረት ግንባር በሚፈጥሩበት ጊዜ፣ በመሃከላቸው የመደብ ትግል አይቆምም፣ ይቀጥላል፣ መልኩና የትግሉ መጠን ግን ይቀንሳል:: ለምሳሌ በመሃከላቸው ያለውን ቅራኔ በጦር መሣሪያ ወይም ከፍተኛ ጠላትነትን በሚያመለክት ፕሮፓጋንዳ አያካሂዱም ነገር ግን ምንጊዜም የማይለወጥ ትግል አለ:: ይኸውም የርዕዮተ ዓለም ትግል ነው::

በተማሪ ማህበሮችም እንዲሁ ነው:: የኢትዮጵያ ተማሪዎች በደፈናው የንኡስ ቡርዧው መደብ ክፍል ናቸው:: ስለሆነም

የንዑስ ቡርዧው መደብ ጠባይ፣ የፖለቲካ አስተሳሰብም ርዕዮተ ዓለም አላቸው:: ነገር ግን ተማሪዎች ከተለያዩ መደቦች የተውጣጡ ከመሆናቸው በላይ የተሰማሩበትም ተግባር (ትምህርት ማለት የርዕዮተ ዓለም ተግባር፣) የተለያዩ መደቦችን ጥቅም ጠበቂዎች የርዕዮተ ዓለም አፈቀላጤዎች ( ideologists ) ለመሆን የሚሰለጥኑበት ነዉ:: ስለሆነም በተማሪዎች መሃከል የርዕዮተ ዓለም ውይይትና ክርክር የዘወትር ተግባር ነው:: በህብረሰቡ ውስጥ ያለው የመደብ ትግል በተማሪዎች ዘንድ ቦግ ብሎ የሚታየው በርዕዮተ ዓለም ትግል መልክ ነው:: በኢትዮጵያ ህብረሰብ ውስጥ የመደብ ትግል ሲፋፋምና፣ አንዳንድ የፖለቲካ ጉዳዮች ከፍተኛ የጊዜው ጥያቄ ሆነው ሲወጡ በተማሪዎች መሃከል ከፍተኛና መራር የርዕዮተ ዓለም ትግል ማስከተላቸው የማይቀር ነው:: የተለያዩ መደቦች የፖለቲካ ፓርቲዎች ባለበት አገር በፖለቲካ የነቁ ተማሪዎች የተለያዩት ፓርቲዎች አባሎች ወይም ደጋፊዎች ይሆናሉ፣ በዚህም ምክንያት በፓርቲዎቹ መሃከል "የህብረት ግንባር" በሌለበት ጊዜ በተለይም በፓርቲዎቹ መሃከል ትልቅ ቅራኔ በሚኖርበት ጊዜ ተማሪዎች የተለያዩ የተማሪ ማህበሮች ሊያቋቁሙ ይችላሉ ተማሪዎች ከህብረሰቡ የመደብ ትግል ውጭ አይደሉምና :: በአገራችን በአሁኑ ጊዜ ተማሪዎችን ሊከፋፍሉ የሚችሉና ተማሪዎች የሚደግፏቸው የታወቁ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሉም:: ስለዚህ ተማሪዎች የሚለያዩበትና ተቃዋሚ ድርጅቶች የሚፈጥሩበት በቂ ምክንያት የለም::



በተጨማሪ የሚቋቋሙት ፓርቲዎችና ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔርያሊስት ከሆኑ የጋራ ጠላታቸውን ለማጥፋት "የህብረት ግንባር" መፍጠራቸው ተገቢና የማይቀር ነውና፣ የተለያዩ ፓርቲዎችንና የፖለቲካ ድርጅቶችን የሚደግፉ ተማሪዎች እንኳ በአንድ በተባበረ የተማሪ ድርጅት ውስጥ የማይቆዩበት ምክንያት የለም::

## I) የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት የአንድነት መሠረት፣

1. የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበሮች ፖለቲካዊ አንድነት መሠረት ፀረ ፊውዳሊዝምና ፀረ ኢምፔርያሊዝም ናቸው::

ማህበሮቻችን አሁን ባሉበት መልክ የአንድ የተወሰነ መደብ ርዕዮተ ዓለም የላቸውም፤ ሊኖራቸውም አይችልም:: የአንድ የተወሰነ ፖለቲካ ፓርቲ ቅርንጫፍ የሆነ ድርጅት ብቻ ነው :: የአንድ መደብ ርዕዮተ ዓለም ሊኖረው የሚችል::

በኢትዮጵያ ተማሪዎች በጠቅላላው የንኡስ ቡርዧው መደብ ክፍል በመሆናቸውና የህዝቡ ጠላቶችም ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ስለሆኑ የኢትዮጵያ ተማሪ በደፈናው በመሠረቱ ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ነው:: የኢትዮጵያ ተማሪ <u>በጠቅላላው</u> ከዚህ አቋም አልፎ ሊሄድ አይችልም:: የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚደግፉና የተለያዩ መደቦችን በይፋ የታወቁ ርዕዮተ ዓለሞችን የሚደግፉ ተማሪዎችና ቡድኖች በአንድ ማህበር ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉት በዚህ

በፖለቲካ አቋም መሠረት ብቻ ነው:: ከዚህ አልፎ ተርፎ፣ የአንድ መደበን ርዕዮተ ዓለም (ለምሳሌ ማርክሲዝም — ሌኒኒዝምን) የማህበሩ ፖለቲካዊ አንድነት መሠረት ለማድረግ መሞከር፣ አብዛኛውን የኢትዮጵያን ተማሪ በጋራ ጠላቶች ላይ እንዳይተባበር መሰናከል መሆን ነው:: አብዛኛው ተማሪ ከአባልነት እንዲሸሽ ማድረግና ማህበሮቻችን በፖለቲካ ንቃትና በርዕዮተ ዓለም ትምህርት የሚያደርጉትን ጥረት፣ አብዛኛውን ተማሪ በአባልነት አጠቃዕለው እንዳያስፋፉ ማድረግም ነው:: ከሁሉም በላይ፣ ለተራማጅ መሣይ አድሀሪዎች በቂ ሰበብ፣ ማርክሲስት— ሌኒኒስት ባይሆኑ ፀረ ፊዩዳልና ፀረ ኢምፔርያሊስት ለሆኑ ተማሪዎችም በቂ ምክንያት፣ ሰጥቶ ሌላ ተፎካካሪ (ተፃራሪ) የሆነ ማህበር እንዲፈጥሩ መገፋፋት ነው::

ውጭ አገር ያሉት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ለውጭ ሰው የሚያሳዩት መልክ አንድ የተወሰነ ርዕዮተ ዓለም (ማርክሲዝም — ሌኒኒዝም) ያላቸው ድርጅት፣ መልክ ነው:: ይህም የሆነው አባላቱ በሙሉ በዕውነት ማርክሲስት — ሌኒኒስቶች ስለሆኑ አይደለም፤ እንደ ዕውነቱ ከሆነ፣ ተሸረርቶ የሚገኘው የንኡስ ቡርዧው ርዕዮተ ዓለም ነው:: የፊዩዳል ርዕዮተ ዓለምም ፎዝሬዥ በሰፊው አለ:: ከዚህም በላይ በፖለቲካ ዝንባሌ በኩል በቅርቡ የንዑስ ቡርዥዋ ፋሽስት ዝንባሌ ብቅ ብቅ ማለት ጀምሯል:: ነገር ግን አብዛኞች ማህበርተኞች ራሳቸውን የሚያዩት በማርክሲስት — ሌኒኒስትነት ስለሆነና በየጉባዔው የሚያሳልፏቸው ውሳኔዎችና በየመጽሔቶች የሚ



ወጡት ጽሑፎችም የዚሁ ርዕዮተ ዓለም መግለጫ በለሚመስሉ ለውጭ ሰው የተሳሳተ መልክ ይሰጣሉ:: በተጨማሪ አስከ ቅርብ ጊዜ ማህበሮችን የመሩት ሰዎች (አውቀትም አሳውቀትም) ማህበሮችን የመሩት እንደአንድ የፖለቲካ ፓርቲ (አንድ ርዕዮተ ዓለም፣ ጥብቅ ዲሲፕሊን እንዳለው ፓርቲ) ወይም እንደ የአንድ ፓርቲ የተማሪ ቅርንጫፍ አድርገው ነው:: ይህም የሚታየው መሪዎች በአብዛኛው ተማሪ ላይ በነበራቸው ከፍተኛ ጥርጣሬና ፍርሃት (“አድሀሪ ነው” በሚል ሰበብ!) እንዲሁም ብዙ ሁኖ መጥቶ ከስልጣን እንዳያወርዳቸው (እነሱ “ማህበሩ አድሀሪ እንዳይሆን” ይላሉ!) በነበራቸው ፍርሀት፣ ምክንያት የነሱን ርዕዮተ ዓለምና የፖለቲካ ዝንባሌ ያልተቀበለውን ሁሉ በጠቃላይ “አድሀሪ” በማለት አብዛኛውን ተማሪ ከማህበሮች ውጭ እንዲሆን በማድረጋቸው ነው:: ስለዚህም ነው፣ በውጭ አገር ያሉት ማህበራት በአንድ በኩል የምርጥ ሰዎች “ ህብረ ሰበዊ ክበብ” የሚመስሉት:: አንድ ህዝባዊ ድርጅት ሊቀበሏቸው ከሚገባው አባሎች ሩቡን ያህል እንኳ ሳይጠቀልል እንዴት ተብሎ ህዝባዊ ድርጅት ይሆናል በአውሮፓ 1000 ያህል ተማሪዎች በአሜሪካ ከ2000 በላይ ተማሪዎች አሉ ይባላል:: የእያንዳንዱ ማህበር አባሎች ግን ከሁለት መቶ አይበልጡም::

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፖለቲካዊ አንድነት መሠረት ፀረ ፊዩዳሊዝምና ፀረ ኢምፔርያሊዝም ናቸው ስለተባለ እነዚህ የፖለቲካ አቋሞች አባልን ለመቀበያ ወይም ለመከልከያ ምክንያቶች ይሆናሉ

ማለት አይደለም። ማህበራችን የተወሰነ የፖለቲካ አቋም ያለው የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የአንድ ግንባር ቅርንጫፍ ባልሆነ በስተቀር በአሁኑ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ በፖለቲካ አቋማቸው ምክንያት ግለሰቦችን አባል እንዳይሆኑ ሊከለክል አይችልም። አባሎችን በብዛት እየተቀበለ ማስተማርና የፖለቲካ አቋም እንዲኖራቸው ማድረግ አለበት። አብዛኛው ተማሪ በፖለቲካ ንቃቱ ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔርያሊስት ባልሆነ፣ ዕውነተኛ ረቮሉሽናዊ የሆኑ ተማሪዎች ረቮሉሽኑን የሚያገለግሉት ከአብዛኛው ተማሪ ሸሽተው ጠባብ የምርጥ ሰዎች ክበብ በመፍጠር ሳይሆን አብዛኛው ተማሪ መሃል ገብተው በመታገል ነው። ሁልጊዜ የማህበሩ አመራር በእኛ እጅ መሆን አለበት በማለት ብቻ አብዛኛውን ተማሪ ማህበር ውስጥ ተባፉይ እንዳይሆን ማድረግ የለባቸውም። የራሳቸውን ማህበር ማቋቋም የሚገባቸው፣ ማህበሩ በአድሀሪዎች ቢያዝና የንግግርና የጽሑፍ ነፃነት፣ ለርዕዮተ ዓለማቸውም የመታገል ነፃነት (ዲሞክራሲ) ሲነፈጋቸው ብቻ ነው። ውጭ አገር ያሉ የኢትዮጵያ ተራማጅ ተማሪዎች ትግል ለኛ ርዕዮተ ዓለም በሰፊው ከማስፋፋት የተሻለ ተግባር ሊሰሩ አይችሉም። አገር ውስጥ ያለው ማህበር ሁሉንም ተማሪዎች በማጠቃለሉ ውጭ አገር ካሉት የበለጠ እንጂ ያነሰ የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም ትግል አላደረገም። እንዲያውም የህይወት መስዋዕትነት ሳለበት ረቮሉሽናዊ ትግሉ በስንት ሺህ



የሚቆጠሩ አባሎችን አሰልፏል። ይህም የተፈጸመው ተራማጆች ሁልጊዜም አመራሩን ካለአንድ ተቀናቃኝ በሞኖፖል መልክ ስለያዙት አይደለም። ስለዚህም ፀረ ፊውዳሊዝምና ፀረ ኢምፔርያሊዝም የተማሪዎች ማህበሮችን ጠቅላላ ይዘት፣ የፖለቲካ አንድነት መሰረት እንጂ ግለሰብ አባሎችን መቀበያና መከልከያ ምክንያቶች መሆን የለባቸውም። ፀረ ፊውዳሊዝምና ፀረ ኢምፔሪያሊዝምን ሁሉም አባል በአንድ ዓይነት እንዲረዳው፣ ሁለቱም የሚጠፉባቸውን መንገዶች ሁሉም እንዲቀበላቸው፣ ሁለቱም ከህብረሰባችን ከጠፉ በኋላ የሚቋቋመውን የፖለቲካና የህብረሰባዊ ስርዓት ሁሉም አባል በአንድ ዓይነት መንገድ እንዲያየው ማሰብ ስህተት ነው። ይህማ የተለያዩ መደቦች ርዕዮተ ዓለም በተማሪው ውስጥ የለም ማለት ነው። ጠቅላላው የማህበሮቻችን አባሎች ከፀረ ፊውዳሊዝምና ከፀረ ኢምፔሪያሊዝም አልፈው የአንድ መደብ ርዕዮተ ዓለምን የፖለቲካ አቋም (ለምሳሌ ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ከወደቁ በኋላ የሰራተኛው መደብ አገዛዝና ሶሻሊዝም መ[illegible]ተሉ [illegible] አይቀርም የሚለውን አስተሳሰብ) ፀረ ፊውዳሊዝምንና ፀረ ኢምፔሪያሊዝምን "በመተርጎም" የማህበሩ የአንድነት መሰረት ለማድረግ መሞከር የማህበሩ አባሎች በሙሉ ማርክሲስት — ሌኒኒስት ይሁኑ ማለት ነው።

2. <u>የማህበሮቻችን ድርጅታዊ አንድነት መሰረት ዲሞክራሲ ነው።</u>

የተለያዩ መደቦችን የሚወክሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች "በህብረት ግንባር" ውስጥ ሲሰለፉ የሚችሉት የአንድነታቸው

መሰረት ዲሞክራሲ ሲኖር ብቻ እንደሆነ ሁሉ፣ የተማሪ
ማህበሮቻችንም (የብዙ መደቦች ርዕዮተ ዓለሞች የሚገኙ
በቸው ድርጅቶቻችን) ድርጅታዊ አንድነት ሊፈጠርና ሊቆይ
የሚችለው ጥብቅና ሰፊ ዲሞክራሲያዊ ግንኙነት ሲኖር ብቻ
ነው:: ይህም ማለት የማህበሮቻችን ድርጅታዊ አቋም አባ
ሎችን ሁሉ በውሳኔና በአመራር ተሳታፊ እንዲሆኑ ሊያደርግ
የሚችል እንጂ አንድ የተወሰነ ትንሽ ቡድን ወይም የአንድ
ሁለት አገር ቅርንጫፍ ማህበሮች ብቻ ከዓመት እስከዓመት
አመራሩን ከላንዱ ተቆጣጣሪ በሞኖፖል እኛኛ ብለው አንቀው
እንዲይዙት የሚያስችል መሆን የለበትም:: ሁለተኛ መሪዎቹ
ግልጽ በሆነ የዲሞክራሲያዊ ስነ ስርዓት፣ ቀጥታና ምስጢራዊ
ድምፅ አሰጣጥ የሚመረጡ መሆን አለባቸው:: ሶስተኛ በማህ
በሩ ውስጥ ማንኛውም አባል፣ ማንኛውም ቡድን (ከአብዛኛው
የተለየ አስተሳሰብ ያላቸው በተለይ) ሀሳቦቻቸውን ለመግለጽ
ሙሉ ነፃነት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል:: የዲሞክራሲ መብት
የተነፈገ ግለሰብ ወይም ቡድን ከማህበሩ ለመውጣትና ሌላም
ማህበር ለማቋቋም መብት እንዳለው ሁሉ፣ የሌሎችን ዲሞክራ
ሲያዊ መብት የነፈገ ወይም የማህበሩን ዲሞክራሲያዊ መሰረት
ሲያናጋ የሚሰራ አባልም ሊባረር ይገባዋል::

አባላቶች የአመራሩን ውሳኔና ተግባር ለመቃወምና ተቃው
ሞአቸውንም በህጋዊና በዲሞክራሲያዊ መንገድ ለመግለጽ፣
መሪዎችንም ምንጊዜም በዲሞክራሲያዊ መንገድ ለመለወጥ ሙሉ



መብት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል:: <u>የዲሞክራቲክ ሴንትራሊ
ዝም የአሰራር ስርዓት</u> የብዙ መደቦችን ርዕዮተ ዓለም
በያዘ ማህበር ውስጥ ወይም ብዙ መደቦችን በጠቃለለ "የህ
ብረት ግንባር" ውስጥ ሊሰራበት አይችልም:: ዲሞክራቲክ
ሴንትራሊዝም በሰራተኛው መደብ የፖለቲካ ፓርቲ (ማለት
አንድ ርዕዮተ ዓለም ያለው፣ በተፈጥሮው ዲሲፕሊን—ወዳድ
በሆነው የሰራተኛው መደብ ፓርቲ) ብቻ ነው ሊሰራ የሚቻ
ለው:: ስለዚህ የተማሪው ማህበርም ከፍተኛ የፖለቲካ ተግ
ባር ያለውና የአንድ የሰራተኛ ፖለቲካ ፓርቲ ቅርንጫፍ
ነው ካልተባለ በስተቀር የድርጅታዊ አንድነቱ መሰረት ዲሞ
ክራሲ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው:: ብዙ ተማሪዎች ከማህ
በሮቹ እንዲሸሹ ካደረጋቸው ምክንያቶች አንዱ በከፊል እንጂ
ማህበሮቻችን ሙሉ በሙሉ ዲሞክራሲያዊ አለመሆናቸው መሆኑን
መገንዘብ አያስቸግርም::

3. <u>በተማሪዎች ማህበር ውስጥ የርዕዮተ ዓለም ትግል አይቆ
ምም ሊደበቅም አይችልም::</u> ተራማጅና ረቮሉሽናዊ ተማሪ
ዎች በርዕዮተ ዓለም የሚያደርጉትን ትግል ካቆሙ ወይም
ከቀነሱ፣ እንደተማሪነታቸው ለረቮሉሽኑ ወይም ለህብረተ ሰቡ
የፖለቲካ እድገት ሊያደርጉት ከሚገባው አስተዋፅዖ ዋናውን
ተግባር ጣሉ ማለት ነው:: የመደብ ትግልም በተማሪው መሃል
የሚገለጸው በዚሁ በርዕዮተ ዓለም ትግል አማካይነት ስለሆነ

ህብረ ሰቡን በጠቅላላው የብዙ መደቦችን አቋም የሚመለከት ትልቅ የፖለቲካ ጉዳይ ወይም የመንግ ሥትን አቋም የሚያናጋ የፖለቲካ ሁኔታ ሲፈጠር በተማሪዎች መሃልም የርዕዮተ ዓለም ትግሉ የተፋ ፋመና መራር መሆኑ የግድ ነው:: ማንኛውም መደብ፣ ማንኛውም ፖለቲካ ነክ ቡድን፣ በተነሳው ታላቅ ጉዳይ ላይ ግልፅ አቋም መውሰድ ይኖርበታል፤ አቋሙን ባይወ ስድ ዝም እንዲል፣ ወይም ድብብስና ሽፋፍኖ እንዲያ ልፍ ተቃዋሚያቹ አይፈቅዱለትም፤ ግልፅ አቋም እንዲ ወስድ ይጠይቃሉ:: ባለፉት ሁለት ዓመታት በኢትዮ ጵያ ተማሪዎች ማህበራት ከፍተኛ የርዕዮተ ዓለም ትግል ተደርጓል፣ አሁንም እንደቀጠለ ነው:: ከትግሉም ጋር ተያይዞ በተ ያች መሃከል ''መከፋፈል'' ተፈጥሮ አል:: በተለይም በአሜሪካው ማህበር ድርጅታዊ መከፋ ፈልን አስከትሏል::

የርዕዮተ ዓለሙ ትግል በይፋ የተካሄደው በአንድ ጉዳይ ላይ ነው:: ይኸውም የብሔሮች ጉዳይ ነው:: መከፋፈሉም የመጣው በዚህ ጉዳይ ላይ የተነሳውን ቅራኔና የአቋም ልዩ ነት ተከትሎ ነው:: በኢትዮጵያ ተማሪዎች ታሪክ ውስጥ... በጣም ከፍተኛና መራር የሆነው የርዕዮተ ዓለም ትግል በብ ሔሮች ጉዳይ ላይ መሆኑና መከፋፈሉም በዚሁ ጉዳይ ላይ መሆኑ የአጋጣሚ ጉዳይ ወይም ሁለት ሶስት ተንኮለኞች ወይም



''የርዕዮተ ዓለም ትግል ማካሄጃ ዘዴዎች ያበላሹ ሰዎች'' የፈጠሩት አይደለም:: ጉዳዩ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ የፖ ለቲካ ስርዓትና ኢኮኖሚ ካናጉት ጉዳዮች ዋናው ይኸው የብ ሔሮች ጉዳይ ስለሆነ ነው:: የገዢው መደብ በስንት ሺህ የሚቆጠር ሰራዊት ያሰለፈው፣ በጀቱ ከዓመት ዓመት የሚና ጋበት ፈሳጭ ቆራጩ ነጋሢ በአገር አገር ነጋ ጠባ የሚን ጦለጦለው፣ ጠላቶቹ ከሚላቸው ጎረቤት አገሮች መሪዎች ጋር ለመስማማት ግዛቱን ቆርጦ የሚሰጠው፣ ሙሉ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲውን የመሠረተው የተጨቆኑ ብሔሮችን ትግል ለመደምሰስ በሚያደርገው ጥረት እንጂ በሌላ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ወይም በሌላ የፖለቲካ ፕሮብሌም ምክንያት አይደለም:: በኢትዮጵያ አሁን ያለው ከፍተኛው የፖለቲካ ፕሮብሌም የተጨቆኑ ብሔሮች ትግል ነው::

ስለሆነም ማንኛውም ይኸንን እንቅስቃሴ የሚደግፍ ተግባር (የተማሪዎች አንዱ ውሳኔ እንኳን ቢሆን) በህዝቡ በተሰማ፣ አዲስ ዓይነት ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ይቋቋም በሚል አርእስት የተጻፈ ሺህ የ''ታጠቅ'' ጽሑፍ የበለጠ የፖለቲካ ውጤት ያስከትላል:: የገዢው መደብም በዚህ አቅጣጫ የሚወስደውን እርምጃና አቋም ከሌላው ጉዳይ የበለጠ ያስፈራዋል:: ስለ ዚህ ማንኛውም መደብ ወይም ፖለቲካ ነክ ቡድንና ግለሰብ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚወስደውን አቋም በሰፊው አውጥቶ አው ርዶ ካሰበ በኋላ የመደብ ጥቅሙን የሚጠብቅለትን አቋም

ይወስዳል:: በኢትዮጵያ ተማሪዎች የተደረገው ርዕዮተ ዓለማዊ ትግልም ይኸንን ቁልጭ አድርጎ አሳይቷል:: የተወሰዱት አቋሞች የተለያዩ መደቦችን ጥቅምና ርዕዮተ ዓለም ያመለክታሉ:: በዚህ ጉዳይ ላይ ውጭ አገር ያሉት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት አባሎች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍለዋል::

1ኛ. የላብ አደሩ ወገን፣

የተጠቁ ብሔሮችን ትግል በኢትዮጵያ ፊውዳሊዝም ላይ የሚደረገው ጠቅላላ ዲሞክራሲያዊ ትግል ክፍል አድርጎ በመቁጠር የተጠቁ ብሔሮችን መብትና ትግል ያለአንዱ ማወላወል የሚደገፋና በልዩ ልዩ ሰበብና ዘዴ ይህንን መብት በመቃወም የፊውዳል ገዢው መደብን ጥቅም የሚጠብቁትን ፀረ ዲሞክራሲያዊ ወገኖችና የንዑስ ቡርዧ ፋሽስት ዝንባሌ ያላቸውን ወገኖች የሚያጋልጥ ነው:: ይህ ወገን ለነፃነቱና ለዘላቂ ዓለም አቀፍ የመደብ ህብረቱ እንጂ ለድንበር የማይቆረቆረውን የላብ አደሩን ወገን ይወክላል::

2ኛ. የዲሞክራሲያዊ ንዑስ ቡርዧ ወገን፣

እነዚህ የተጠቁ ብሔሮችን መብት በማወላወልና በግማሽ ልብ የሚደግፉ ናቸው:: በናተኛ የፊውዳል ርዕዮተ ዓለም ተፅዕኖ ስላለባቸው በብሔር የበላይነት በሚት ያላቸውን (ሸቪኒስቶችን) ግልፅ በግልፅ ወጥተው በመቃወም ፈንታ ባልሆነ ቦታ "የተማሪ አንድነት" የሚል መሪ አባብ(slogan) በማምጣት የፊውዳል ጥቅም ጠባቂ የሆኑትን ሸቪኒስቶችና



የንዑስ ቡርዧ ፋሽስት ዝንባሌ ያላቸውን ወገኖች እንዳይደክሙ ጠለሳና መከታ የሚሰጡ ወገኖች ናቸው:: በተጨማሪ ተማሪ የተከፋፈለበት ጉዳይ ይኸው ቢሆን ክፍፍሉ በሌላ ጉዳይ ላይ እንደሆነ በማስመሰል የጉዳዩን አውራነት ዝቅ ለማድረግና ትግሉን በሌላ አቅጣጫ ለመምራት የሚጥሩ፣ የላብ አደሩ ወገን በሸቪኒስቶች ላይ ሳደረገው ርዕዮተ ዓለማዊ ትግል፣ የቀረቡትን ጽሑፎች የጻፉትን ጓዶች የትግል ዘዴ አያውቁም በሚል ሰበብና በሌላ ጥቃቅን ምክንያት "በመዝጊያ ስንጥቅ ገብቶ ምሰሶውን ለመንቀል መሞከር" የሚባለውን ከንቱ ዘዴ ሥራ ላይ በማዋል በሸቪኒስቶች አንገት ላይ የተጋደመውን ሰይፍ ለማደልደም ይጥራል:: ይህ ወገን በሌላም ጉዳይ (በተለይ ገና በይፋ ባልወጣውም የድርጅት ጉዳይ ላይም) እንደሚያሳየው፣ በህዝቡና በሰርቶ አደሩ ወገን ሙሉ እምነት የሌለውና የሚመጣውንም ህዝባዊ ረቮሉሽን ሙሉ በሙሉ አቅፎ ያልተቀበለ፣ የፊውዳሊዝምን ኃይል የሚያጋንን ስለሆነ ብዙ ያወላውላል:: ሆኖም ይህ ወገን ወላዋይ በመሆኑ የረጋ መልክ የለውም፣ በውስጡም ወደ ላብአደሩ ወገን በጣም የሚቀርቡ ጓዶች አሉበት::

3ኛው ወገን የሁለት ክፍሎች ህብረት ነው፣

አንዱ ወገን ጠርቦ የፊውዳል ገዢ መደብ ወገን የሆነና በዚሁ በብሔሮች ጉዳይ ላይ ከገዢው መደብ ጋር አንዱ ዓይነት አቋም ያለው ቢሆን ሌላው ወገን ግን የፋሽስት ዝንባሌ ያለው የንዑስ ቡርዧ ክፍል መደብ ወገን ነው:: የፊውዳል

ወገን የሆነው ክፍል አብዛኛው በይፋ አቋሙን የማይገልጽ በደባባይ ወጥቶ መከራከር የሚፈራ ሲሆን፣

ጥቂቱ ግን የፋሽስት ንዑስ ቡርዧውን ወገን እየገፋፉ ቃሉን እየደገሙና እያስተጋቡ በሱ ከለላ የሚኖር ወገን ነው:: ሁለቱም ክፍሎች በብሔሮች ጉዳይ ላይ አንድ ዓይነት አቋም አላቸው፣ የብሔሮችን የመገንጠል መብት ይቃወማሉ የንዑስ ቡርዧ ፋሽስት ወገን የሆኑት ጥቂቶች ሲሆኑ አብዛኞችም የሚገኙት ሰሜን አሜሪካ ነው:: ይህ ወገን በሌላ በሶስተኛው አገሮች እንደተፈጸመው ሰርቶ አደሩ ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝምን ሲደመስስ ሲነሳ የሰራተኛው መደብ ፓርቲ በሌለበት ወይም ባልጠነከረበት ቦታ የህዝቡን እንቅስቃሴ አመራር በልዩ ልዩ ዘዴ በመውሰድ "በአንድነትና" በህብረት ስም የሚቀጋውን ሰርቶአደሩና ፓርቲውን ዲሞክራሲያዊ መብት ነፍጉ የሚጠፋፋውንና የሚጠቁነውን ፋሽስታዊ የንዑስ ቡርዧ መደብ ይወክላል:: ካፒታሊዝም ባልጠነከረበት አገር በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም ላይ ህዝባዊ ጦርነት ሲደረግ ወይም የቀጥታ ቅኝአገዛዝ ተሸሮ አዲስ ዓይነት ቅኝ አገዛዝ በተተከለበት ቦታ የረቮሉሽናዊ ድርጅትን ወይም የመንግሥትን አመራር የሚይዙት የንዑስ ቡርዧ መደብና የቡርዧ ክፍሎች ደካማና ካለዘመናቸው አመራር የወሰዱ



ስለሆኑና በፖለቲካ የበሰለው ስልጣን መውሰድ ጊዜው የሆነውን የላብ አደሩን ወገን በጣም ስለሚፈሩት ትንሽ ዲሞክራሲ እንኳን ሊሰጡት አይችሉም፤ በናካቴው የፋሽስት ጭቆና ያወርዱበታል:: በተማሪ ማህበራችን ብቅ ብቅ ማለት የጀመረው የንዑስ ቡርዧ ፋሽስት ዝንባሌ ያለው ወገንም እንዲሁ "በአንድነት" ስም ፀረ ዲሞክራሲያዊ የሆኑ አቋሞችን ይወስዳል፣ ፀረ ዲሞክራሲያዊ ተግባሮችን ይፈጽማል:: በተማሪዎች ማህበራት ውስጥ እስከ ዛሬ ያሳየውን ፀባይ እንመርምር::

ሀ) እንደ ወጣቱ ሙሶሊኒ የሰራተኛውን መደብ ርዕዮተ ዓለም አቀበላለሁ ይላል "ማርክሲዝም—ሌኒኒዝም ማኦ ቤ ቶንግ ሀሳብ" ነው ሀይማኖቱ አያለ በየአደባባዩ፣ በየስብሰባው ወዘተ ይለፍፋል፤ በየወረቀቱ ይጫጭራል::

ለ) በዚሁ መከረኛ "ማርክሲዝም—ሌኒኒዝም ማኦ ቤ ቶንግ ሀሳብ" አመሃኝቶ የብዙ መደቦች ርዕዮተ ዓለምና የፖለቲካ ዝንባሌ ያላቸውን ተማሪዎች የስስት አራት ሰዎችን ጥራዝ ነጠቅ አስተባብሮ፣ ፀረ ረቮሉሽናዊና ፀረ ዲሞክራሲያዊ ተግባር አለአንድ ጥያቄ ተቀበሉ ይላል:: ማህበርተኞች በስማቸው ለጓደኞቻቸው ገንዘብ ቢሰበስቡ "ዲሞክራቲክ ሴንትራሊዝምን ጣሳችሁ" በማለት "ከማህበሩ አስወጣችኋለሁ ይላል::

ሐ) አሜሪካ ዩኒቨርሲቲያች ውስጥ ቆዩ ብሎ፣ ብሔራዊ ጭቆናን በመቃወም በየተራራውና በየሸንተረሩ፣ በቆላውና በደጋው፣ ደማቸውን የሚያፈሱትን የኤርትራንና የባሌን የአፋሲን፣ የሐረርን የኦጋዴንን ህዝቦች በ "ፕሮሊታርያን ኢንተርናሽናሊዝም" ስም የፖለቲካ ድርጅት ወሬ እንኳን በሞቶ ከማያውቀው የኢትዮጵያ የሰራተኛ መደብ ጋር አንድ ፓርቲ "ካልፈጠራችሁ ደማችሁን በማፍሰስ የምትታገሉለትን መብት ሙሉ በሙሉ አላውቀላችሁም" ይባል:: እንደእውነቱ ይህ ወገን የሚያልመው ብስት በራተኞችና አምስት ገበሬዎች እንኳ ባያደራጁ (እንኳን ሁሉ ታጥቆ ጠበንጃ) ሲያነብ የኤርትራና የኦሮሞ ህዝቦች "ና ምሬን" ("አንድ ድርጅት እንፍጠር" ")እንዲሉት ነው::

ይህ ፀረ ዲሞክራሲያዊ የሆነው የነውስ ቡርዧው ጠሌነት ነው::

መ) አብዛኛው ተማሪ የፀረ ዲሞክራሲ "አንድነት" ጥሪውን እንቀበልም በማለት፣ የኛ አንድነት እስተባሰብ የህዝቦቻችን አንድነት በእኩልነት በመተማመን በዕውነተኛነት ወንድማማችነት የተመሰረተ የጋራ ጠላትን በመዋጋት በሚፈስ ደም የሚገነባ ዘላቂ የላብ አደር ወንድማማችነት ነው" ሲለው "የፕሮለታርያን ጥቅም ሸጣችሁ "በማለት ዲሞክራሲያዊ



ማህበሩን አፍርሱ፣ ገንዘቡን ሰርቁ በእብሪት በብዙኃን አባሎች ማህበር ስም ይጠቀማል::

ሠ) በዲሞክራሲያዊ መንገድ ታገል፤ አብዛኛው ተማሪ አስተሳሰብህን እንዲቀበል በዲሞክራሲያዊ ማህበር ውስጥ ገባ፣ ሲባል መሪነቱን ካላስረከባችሁኝ ይላል:: በዲሞክራሲያዊ መንገድ በሚደረግ ትግል ፈጽሞ ሀሳብ የለውም::

የመደብ ትግል እየከረረ የፊውዳል መደብና የጥገኛ ቡርዧዚው እየተዳከመ ሲሄድ፣ ኃይሉና የሠራተኛ መደብ ድርጅት ከሌለ የኢትዮጵያ ነውስ ቡርዧ መደብ የህዝቡን ትግል ለመምራትና የመንግሥት ኃይል ለመጨበጥ ያለው ምኞት እንደገና አመራር ለመያዝ ያለው ዕድል እየጐላ ሲሄድም የፋሽስት ዝንባሌው እየጠነከረ ሲሄድ ይችላል:: ከህዝቡ ትንሽ ተቃውሞ፣ ትንሽ የተለየ ሀሳብ ሲ ያጋጥመው "በአንድነት" ("ብሔራዊ አንድነት" ..ወዘተ) ስም ህዝባዊ ተቃዋሚዎችን ይረሽናል:: አሁን በተማሪም ማህበር ውስጥ ያሉትም የነውስ ብርዧ ፋሽስት ወገን ትናንት "አንድ ብሔር እንድንፈጥር የትግል አንድነት" ሲሉ ቆይተው "ወደፊት አንድ የኢትዮጵያ ብሔር መፍጠር" የሚለው ሀሳባቸው ትርጉም ቢያጣ "የሰራተኛው መደብ አንድነት" በሚል ስም የማህበር

ገንዘብ ይሰርቃሉ፣ የግል ደብዳቤ ይበርቃሉ፣ ጠላ ቶቻችን በሚሏቸው ሰዎች ላይ የፈጠራ ወሬ ያስወራሉ:: "የምስጢር ድርጅት" አሳቻው በማለት ሰንይለ ሥላሴ በመጽሔት ያስጠነቅቃሉ:: በጭፉ እነርሱም እንደአቅ ማቸው "ይረሽናሉ":: ወይንም ለማስረሸን አስል ፈው ይሰጣሉ::

እንገዲያውስ፣ የተማሪዎች ማህበሮቻችን የተከፋፈ ሉት በብሔሮች ጉዳይ ቢሆን የተከፋፈሉት አሳይ በተ ጠቀሰው መንገድ እንጂ የኢ..ኢ.ተ.ማ ~የሉንዱ ቅርንጫፍ ማህበር (ማለት የኢ.ኢ.ተ.ማ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ) በሚያዝያው "የታጠቀ" እትም እንደ ገለጹት አይደለም ያንን እትም ልብ ብለው ያነበቡ የኢ.ኢ.ተ.ማን መሪዎች የቆየ አቋም የማያውቁ ሰዎች የሉንዱ ጓደኞች በየትኛው ክፍል እንደሚመደቡ መወሰን አያስቸግራቸውም::

በመጠረሸ ስለትንተናችን አንዱ ቃል መጠመር አለ ብን:: ይህን አከፋፈል ቋሚ የመደብ አከፋፈል አድ ርጉ መቁጠር አስቸጋሪ ነው:: ምክንያቱም 1ኛ) ይህ ክፍፍል የመጣው ምንም እንኳን በአንዱ በአውራ የፖለ ቲካ ጉዳይ ላይ ቢሆንም፣ አንዱ የፖለቲካ ጉዳይ ብቻ በመሆኑ በተማሪው (በተለይም "የግራ ክንፍ" በሚባለው) ውስጥ የሚኖረውን ዘላቂ መከፋፈል ሊያመ ለክት አይችልም:: 2ኛ) ተማሪው የሚኖርበት ጊዜያዊ



የኑሮ ሁኔታ ጊዜአዊ ( trasitional ) ከመ ሆኑ በላይ አቋማቸው የታወቀ የመደብ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሌሉበት በአገራችን ያሉ ተማሪዎች የሚ ወስዱት የፖለቲካ አቋም የተጠበጠ አንዱ የፖለቲካ ውጤት ስለማያስከትል በቃልና በጽሑፍ የሚገለጽ "አቋም" ሁሉ መመለሸ እንደሌለው አቋም(com- mitment) ሊወስዱ አይቻልም:: ለፊትና "አን ደሰው ልሁን" በማለት 'አቋም' የሚወስዱ አሉ:: ስለዚህ ለወደፊቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቢቋቋሙና ሌሎች ዓበያትና ትኩስ የፖለቲካ ጉዳዮች ቢነሱ አሁን በሚታዩት ወገኖች ውስጥ ካሉት ክፍሎች ብዙ ዎቹ ዐውነተኛና የመደብ አቋማቸውን በሚገልጹባቸው አዳዲስ ወገኖች ይከፋፈላሉ:: በተለይ ወላዋይ በሆነው ክፍል ውስጥ ያሉት ጓደኞች በቅርቡ አቋማቸ ውን መለየታቸው የማይቀር ጉዳይ ነው::

II) የፊውዳል ርዕዮተ ዓለም ተጽእኖ፡

የፊውዳል ርዕዮተ ዓለም አሁንም በተማሪዎች ህሊና ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለው:: በኢትዮጵያ ህብረተሰብ የተገበ ራረው የፊውዳል ርዕዮተ ዓለም በመሆኑ በኢትዮጵያ ተማሪ ዎች ህሊና አሁንም ተፅዕኖውን እንደጣለ ቢገኝ የሚደንቅ ነገር አይደለም:: የሚደንቀው "የግራ ክንፍ" በሚባ ለውና ከፍተኛውን ረቮሉሺነሪ ርዕዮ ዓለም ተቀብሏል

በሚበለው ወገን ያለው ተፅዕኖ የቶን ያህል ትልቅ
መሆኑ ነው:: በግራ ክንፉ ያለውን ከበዱ ርዕዮተ
ዓለማዊ ጉድለት ያጋለጠው ባለፉት ሁለት ዓመታት የተ
ካሄደው የርዕዮተ ዓለም ትግል ነው:: የፊውዳል ርዕ
ዮተ ዓለም በብዙ መንገዶችና አቅጣጫዎች ታይቷል::

1ኛ) በተማሪዎች ውስጥ ለተነበው የርዕዮተ ዓለም
ቀሪነ <u>በፊውዳል የፖለቲካ ትግል ዘዴዎች መጠቀም፣
የረቮሉሽናዊ ግብረ ገብነት</u> ( morality )
<u>ጠርሶ መጥፋት፣</u>

1፡ በርዕዮተ ዓለም ትግል የተቃዋሚ ወገን ሆነው
የተነሱት ሰዎች በሚያቀርቡት ሐሳብ ላይ በግል
ጸና በይፋ አጥጋቢ ክርክር አቅርቦ የራስን አቋም
በመግለጽ ፋንታ ሐሳቡን በቀረቡት ሰዎች ላይ ስለ
ግል ታሪካቸውና ጠባያቸው ሐሜትና የሐሰት ወሬ እየ
ፈጠሩ ማስወራት፤ በቀረበው ሐሳብ ትክክለኛነት
ወይም ስህተተኛነት ሐሳብ በማቅረብ ፋንታ በርዕዮተ
ዓለም ወደኋላ የቀረውንና ከፊውዳል ርዕዮተ ዓለም
ያልወጣው ተማሪ የሚፈራውን ነገር የፀሐፊዎቹ ውስ
ጣዊ (የተደበቀ) ዓላማ አስመስሎ በማስወራት ስለ
ተቃዋሚዎች ሁኔታና ኑሮ የሆነ ያልሆነ ወሬ ማስ
ወራት — እነዚህ ሁሉ በተማሪው ህሊና ላይ የተቃ



ቃሚውን ወገን የሚያጥላላና የሚያጠራጥር አስተ
ሳሰብ ቀርፀ የሚያቀርበበትን ሐሳብና ክርክር
እንዳያነብ፣ እንዳያዳምጥና እንዳይቀበል ለማድረግ
ነው:: በዚህ ዘዴ ሊጠቀሙ የሚችሉ በህዝቡ ላይ
ከፍተኛ የንቀት አስተሳሰብ ያላቸውና አስተውሎ
ትክክለኛን አቋም ሊወስዱ ይችላል ብለው ከማያምኑ
ፀረ ዲሞክራሲያዊ የሆኑ የፊውዳል ፖለቲከኞች ብቻ
ናቸው:: ከዚህም በላይ እነዚህ የፊውዳል ፖለቲ
ከኞች በጽሑፋቸው ውስጥ የተቃዋሚዎቻቸውን "ዕው
ነተኛ" ገላዊ ታሪክና ሁኔታ የሚያመለክቱ አስመ
ስለው የአሽሙር የምፀትና የውስጠ ወይራ ገለጻዎችን
ይጠማምራሉ::

ባለፉት ሁለት ዓመታት የበላዩ፣ የአድሀሪው፣
"ተማሪ ፖለቲከኛ"፣ የረቮሉሽናዊው መሳይ ምሁ
ራን፣ የፊውዳል መደብ ጥገኞች ሐሜት፣ አሽሙር፣
ስድብና ጥላቻ ማውረጃ ከሆኑት ወገኖች የማህበራ
ችን አባሎች በጥቅል ወይም በግል ይገኙበታል::
እስከዛሬ ዘለፋቸውን፣ የጥላቻና የስም ማጥፋት
ዘመቻቸውን ችላ ብለነው ኖረናል:: አሁን ግን
ለሚሰነዘርብን ስድብና ዘለፋ ምንም መልስ አለመ
ስጠታችን እነዚህን ርካሽ የፊውዳል ፖለቲከኞች
በይሉኝታ ዝም ሊያሰኛቸው ቀርቶ መሰረት የሌለ
ውን ወሬአቸውን ከናባቴው ውቅያኖስ አሸጋግረው
ማዛራት ጀምረዋል::

እንደዎ " በቪላ ውስጥ ይኖራሉ " ይሉናል፣ እን ደዎ " ሁሉም ትግሬዎች ናቸው " የሚል ወሬ ያሰፋፋሉ፣ እንደዎ " አምስቱ ትግሬዎች የተቀሩት ሌሎች ናቸው " የሚል ወሬ ያነባሉ፣ ቢያስናቸው " ሁሉም ከአልጂሪያ ሄደዋል የቀሩት ሶስት ትግሬዎች ናቸው " ይላሉ፣ ይገረም ብለው " የትግራይ ትግርኚ ገንበር ሊከፍቱ ነው" ይሉናል:: ዋናው ነገር ስለኛ ወሬ በተነሳ ቁጥር የሚወራው ሁላችንም ወይም አብዛኛዎቻችን ትግሬ ዎች መሆናችን ነው:: ይህ የሸቪኒስቶችንና የአድሀሪ ዎችን ፀረ ትግሬ ጥላቻ ለማነሳሳት የሚነዛው ወሬ እንዳልበቃ ሁሉ ይበስ ይበስ ብለው " የብሔሮችን ጉዳይ " (የተጨቆኑ ብሔሮችን የመገንጠል መብት) " የደገፉት በኤርትራ ገብተው ትግሬ ውስጥ የጦር ትግል ሲጀምሩ ስለፈለጉ ነው " አሉን! ሁሉንም የፖ ለቲካ አቋም " ለታክቲክ " ተቀብለው፣ ሲመቻቸው ደግሞ " ለታክቲክ " ከመባል በስተቀር ምንም ዓይነት የፖለቲካ እምነት የሌላቸው የፊውዳል ፖለቲከኞች ያስ ነዛብንን ወሬ ዘርዝረናል:: በዚህ ጉባዔ አዳራሽ ከሉና ያስወሩትን የሚያምኑበትና ዕውነት ነው፣ ወይም መጥፎ ዓላማ የለበትም የሚሉ ከሆነ፤ ይነሱና ይደግፉት:: አለዚያ የጉባኤው ተካፋዮች እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ቢያጋጥሟቸው በሳይ ወይም የፊውዳል ገዥዎች መሣሪያ ብለው እንዲሰይሙልን እንጠይቃለን::



በኛ በኩል ግን የሚያስፈልገበት በታና ሁኔታ የተወለድንበትን ብሔር ብንገልጽም፣ በሁኑ ሁኔታ የምንገልጽበት ምክንያት የለንም:: ዘራችንን " ካሳወቁሁ " የሚል ካለ፣ የመንግሥቱ የፀጥታ ክፍል ዶረስ ሄዶ ዘር ማንዘራችንን ይቁጠር! ነገር ግን እዚህ ለመጥቀስ የምንፈልገው በአድሀሪው መንግ ሥት የተሰጠን ስምና የተወነጀልንበት ሀጢአት ቁጥር ልክ ባይኖረውም፣ ለአንዱ ለተወሰነ ብሔር ጥቅም ብቻ የምንታገል መሆናችንን ለማመልከት ሲል ስለቡድናችን አባሎች 'ዘር' (ብሔር) እንዱም ወሬ በአዲስ አበባ ሲያስወራ እንዳልደፈረ ነው:: በተረፈ አብዛኛዎቻችን ቀርቶ፣ ሁላችንም ከማንኛውም ብሔር (ትግሬ፣ አደሬ፣ ወሳሞ፣ ኦሮሞ፣ ወዘተ) ናቸው ብንባል ወይም ከሁሉም ብሔሮች የተውጣጡ ናቸው ብንባል ልዩነት የለውም:: ሁላችንንም የሚያቀራርበን የፖለቲካ እምነት በኢትዮ ጵያ ካሉት ብሔሮች ከመጡ ጓዶች ጋር ብቻ ሳይሆን ከሌሎችም አገሮች ብሔሮች ከፈለቁ ጓዶች ጋር ያስተ ባስረናል::

ነገር ግን፣ ወሬው የተነዛው ለተወሰነ አላማ ነው፤ በተማሪው ህሊና ውስጥ ባለው የፊውዳል አስተሳሰብ በመ ጠቀም በእኛ ላይ ጥርጣሬ ለማስፋፋትና የምናቀርበውም ሐሳብ ተቀባይ እንዳያገኝ፣ ከተራማጅ ኢትዮጵያውያን ጋር

እንዳንተባበር ለማድረግ ነው:: የፊውዳል ገዢው መደብ በኢትዮጵያ ህዝብ ህሊና የቀረበው የፖለቲካ አስተሳሰብ ወርሶ የተጣመመና የተሳሳተ ነው:: በኢትዮጵያውያን የፊውዳል መደብ አገዛዝ ለመሸፈንና ሠርቶ አደሩን ህዝብ ለመከፋፈል ፖለቲካን የፖለቲካ ኃይልንና የመንግሥት ስልጣኑን ሁሉ ከንጉሡ ዘውድና ከአንድ ብሔር ጋር ያያይዘዋል:: ንጉሡ ነገሥቱ ከአማራ ብሔር መሆኑን መሠረት በማድረግ የአማራ ብሔርን ገዢ፣ የተቀሩትን ብሔሮች ተገዢ አድርጎ ያቀርባቸዋል:: ከዚህም አያይዞ፣ በንዱ በኩል፣ ማንኛውም የፖለቲካ ለውጥና ተቃውሞ ሲነሳ፣ የንጉሡን ዘውድ ብቻ ለመውሰድ የሚነሳ ትግል ሲያደርገው፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ማንኛውም ለውጥ የአማራን ብሔር አገዛዝ ለውጦ የሌላውን ብሔር ገዢ ለማድረግ የሚደረግ ለውጥ ያስመስለዋል:: በፖለቲካ ያልበሰለ (የመደብ ንቃት የሌለው) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ (አማራም ሆነ ሌላ) ስለፖለቲካ ያለው አስተሳሰብና ፊውዳሊዝም ለህዝቦችን ያስተማረው የፖለቲካ " ዕውቀት " ከዚሁ አያልፍም::

ይኸንን ለመገንዘብ የሚጨና ቁለማ መሪዎች ልክ እንደ ታሰሩ መላውን አገር እንደሰደድ እሳት ያቀጣጠለውን፣ በቀልድ መልክ የተሸረፈን ዐረ ኦሮሞ ፕሮፖጋንዳ ማስታወስ ይበቃል:: በሸሺኒሳት የንቀት መንፈስ የኦሮሞን



ህዝብ ለማጥላላትና ለማዋረድ አንጂኔራል ታደሰ ብሩ የባንዲራቸው አርማ " በሬ " (" ቆቲቆ ") ነበር ብለው ካስወሩ በኋላ፣ በባንዲራቸው ላይ " ቆባ ቆቲቆ ዘአምነገደ ኦሮሞ " ብለው ጽፈው ነበር የሚል ወሬ ባንዴ ተነዛ:: (ማስታወስ ያለብን በደግም ሆነ በክፉ፣ ስመጥር የሆነ ግለሰብ ስም ሲነሳ፣ የሚጠቀሰው የሰውዬው ብሔር መሆኑንና፣ የሰውዬው መሞገስ ወይም መዋረድ ከብሔሩ መሞገስና መዋረድ እንደማይለይ ነው) የተነዛው የሀሰት ፕሮፖጋንዳ የፖለቲካ ዓላማ ግልፅ ነው እዚህ ላይ ለመጥቀስ የምንፈልገው ግን ፕሮፖጋንዳው የቀረበበትን መልክ ነው:: ስልጣን ሊወስድ የፈለገው፣ አንድ ብሔር ፣ (ኦሮሞ)፣ በስልጣን የሚወርደውም፣ ሌላ ብሔር፣ (አማራ) የፖለቲካ ስርዓቱም ስ ይለውጥ ያው የነጋሲ አገዛዝ (ቆባ ወዘተ) እንደሆነ በሚገልጽ መልክ ነው የቀረበው:: በዚያን ጊዜ በመንግሥቱ በላዮች ይነዛ ከነበረው ወሬ ሁሉ "ሬቶብሊክ" የሚለው ቃል አለመኖሩ አድሀሪው መንግሥት ህዝቡ እንዲረዳ የፈለገው " ጋሎች ጋላ ሲያነግሡ ነበር " የሚለውን ወሬ ብቻ እንደሆነ ያመለክታል:: ህዝቡ የተባለውን ፕሮፖጋንዳ አመነውም አላመነውም፣ " ቀልዱ " ሊገባው የቻለው፣ በለው የፖለቲካ እውቀት ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ነው::

አድህሪው መንግሥትና የፊውዳሉ የገዥ መደብ በት·ግረ ብሔርና ከዚህ ብሔር በወጡ ተራማጆችና ረቮሉሽናውያን ላይ የሚያስፋፉው የጥላቻ፣ የጥርጣሬና የማስፈሪያ ፕሮፓጋንዳም ከመሰረቱ ያው ነው:: ግን በትግረ ብሔር በመጡ ጊዶች ላይ የሚደረገው ፕሮፓጋንዳ የተለየ የራሱ መልክ አለው:: የዚህም ምክንያት፣ 1ኛ ህዝቡ በጠቃላይ " ትግረ " የሚለው በከፊል፣ በደንቋውና በባህሉ፣ ከትግረ ህዝብ የማይለየው፣ የኤርትራ ህዝብ የሚያደርገው ትግል በፊውዳሉ መደብ ታላቅ ፍርሃት ለቆበታል:: ስለዚህ የአዲስ አበባ ተማሪዎች ስላማዊ ስልፍ በደረጉ ቁጥርና መንግሥቱን በተቃወሙ ቁጥር ከመሪዎች ውስጥ አንዱ ትግሬኛ የሚናገር ባለ (በኤርትራ ይሁን በትግረ) የተማሪውን ተቃውሞ " የትግሬዎች ሴራ " በማለት ፕሮፓጋንዳ ከመንዛት ሌላ ትግሬኛ የሚናገሩትን ሁሉ " የኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባር ወኪሎችና ሰላዮች ናቸው " እያለ ከመሰየም በዝና አያውቅም:: 2ኛ ከፊውዳሉ መደብ ኃይለኛውና ትልቅ ጥቅም ያለው የሸዋው ክፍለ ግዛታዊ የበላበቶችና የመሳፍንት ቡድን ለንጉሡ ዘውዱ ዋና ተቀናቃኝ አድርገው የሚቆጥረው የትግረውን የባላባቶችና የመሳፍንት ቡድን ስለሆነ፣ ለዚሁ ቡድን ያለውን ጥላቻና ፍርሃት የሚገልጸው በትግረ ብሔርና በተራማጆች



ላይ የጥላቻ፣ የጥርጣሬና የማስፈራሪያ ፕሮፓጋንዳ በመንዛት ነው:: ስለዚህም ማንኛውም ተራማጅና ረቮሉሽናዊ ትግረ ጊዶ ላይ የሚነዛው የጥላቻና የጥርጣሬ ፕሮፓጋንዳ የማያቋርጥና ብዙ መልክ ያለው ነው:: ይህ ፕሮፓጋንዳ ስር የሰደደ ከመሆኑ የተነሳ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝቦች (በተለይም ለሰርቶ አደሩ) ነፃነትና ደህንነት የኢትዮጵያ ተራማጅና ረቮሉሽናዊ ተማሪዎች በሚያደርጉት ትግል የትግረ ተማሪዎች ያፈሰሱት ደምና ከትግረ ብሔር የፈለቁ ረቮሉሽናዊ የተማሪ መሪዎች ያደረጉት የመጨረሻው መስዋዕትነት (የህይወት) እንኳ ገና ሊለውጠው አልቻለም::

የመንግሥቱ ሰላዮች፣ አድህሪዎችና <u>ስለጊዜአዊ ቅራኔ እንጂ ስለዘላቂው ረቮሉሽናዊ ዓላማ ማሰብ የማይችሉ</u> " የተማሪ ፖለቲከኞች " በኛ ላይ የሚያስፋፉትን ወሬ መመልከት የሚገባን በዚህ አቅጣጫ ነው:: የኛ ማህበርና የማህበራችን አባሎች የሚያደርጉትን ርዕዮተ ዓለማዊ ትግል በቀጥታ መንገዱ መቋቋም ቢያቅታቸው፣ በዝቅተኛና ርካሽ በሆነው የፊውዳል የፖለቲካ ትግል ዘዴ በመጠቀም ሊያጠቁን መሞከራቸው ነው:: ይህንን አድህሪና ወራዳ የፊውዳል ዘዴ የላብ አደር ኩራትና ግብረ ገብነት ባልተለየው ረቮሉሽናዊ ሐቅ እንቋቋመዋለን እንጂ አላማችን ከቶ አይዘነፍም፣ ከጠር ጫዳ ፈጽሞ አናፈገፍግም::

2. "በገራ ክፍል" ርዕዮተ ዓለም ውስጥ የላብ አደሩና የረቮሉሽናውያን ገበሬ ገዢነት ምንም ቦታ የሌለው መሆኑን ካበዓን ሁኔታዎች ውስጥ ሁለት ነገሮች ጉላ ብለው ይታያሉ::

ሀ) የመጀመሪያው አምና የአሜሪካን ማህበር ፕሬዚዳንት የነበረው ሰናይ ልኬ "ESUNA BI-MONTHLY" የተባለ መጽሔት በማውጣት የፈጸመው ህገ ወጥና ፀረ ረቮሉሽናዊ ተግባር ነው:: በመጀመሪያ ነገር ይህ ሰው አለአንዳች ምክንያትና አለአንዳች ህጋዊ ማስረጃ በአልጀሪያ የምንገኘውን በጥቅል ይወነጅላል:: ቅጥ የሌለው ዘለፋውን ያወረደብን፣ መሰረት የሌለው ክሱን የሰነዘረብን በጥላሁን ታከለ ስም ከዚህ ቀደም የአሜሪካው ማህበር መሪዎች በነበሩት በሐጎስ፣ በእንድርያስ...ወዘተ ላይ በበሴሮች ጉዳይ ላይ የቀረበውን ርዕዮተ ዓለማዊ ክርክር "ጽፈዋል" በሚል መነሾ ነው:: ይህንን ወሬ ከየት እንዳመጣው የሚያውቀው እሱ ብቻ ነው:: ከሁሉ በፊት ጥላሁን ታከለ የሚባል ሰው አናውቅም፣ በማህበራችንም ውስጥ የለም:: ጥላሁን ታከለ የተባለው ሰው ስም ማንም እንደሚጠረጥረው የብዕር ስም ይመስለናል:: ደራሲው ያንን ጽሑፍ በብዕር ስም ያወጣበት በቂ ምክንያት ባይኖረው አይቀርም::



ጽሑፉ የሐሰት ወሬ የሌለበት ከመሆኑም በላይ የታወቁ ሰዎች በግልፅ በወጡት ጽሑፍ ላይ ብቻ የተገለጸውን ሐሳብ ስህተተኛነት ከማሳየትና ደራሲያቸውም በነዚያ ጽሑፎች በወሰዱት አቋም ብቻ ሊሰጣቸው የሚገባውን መታወቂያ ለአንባቢያች ከመግለጽ አልፎ ተርፎ ስለሰዎች የግል ታሪክ ወይም ፀባይ (ስለጻፉት ሌላ ጽሑፍ እንኳን) አንድ ቃል አይጠቅስም:: ስለዚህ የደራሲውን ብሔር፣ ሃይማኖት፣ የትምህርት ደረጃ፣ ዕድሜ ወይም ወርዱና ቁመት ካላወቁ በስተቀር የቀረበውን ጽሑፍ ትክክለኛነት ወይም ስህተተኛነት ብቻ አይቶ አቋም መውሰድ የማይችል (የማይፈልግ) ሰው ካልሆነ በስተቀር፣ ሌላ ሰው ጥላሁን ታከለ የተባለውን ሰው ማንነት ለማወቅ ጥረት ለማድረግ የሚያነሳሳውን ዓላማና ማናቸውም ጥቅም አይታየኝም:: የሐሰት ወሬ ከጻፈ ወይም ስም ካጠፋ ግን፣ ወይ ጽሑፉን በሚያነቡት ሰዎች ወይም ጽሑፉን ተቀብሎ ባተመው ሰው አማካይነት ሊጋለጥ ይገባዋል:: የተጻፈውን ጽሑፍ በመተንተን ብቻ ባይወሰን፣ አላግባብ የሐሰት ወሬ ነዝቷል ከተባለና ማንነቱን እንዲገልጽ ከተጠየቀ ጥላሁን ታከለ ማንነቱን ለመግለጽ ወደኋላ እንደማይል እናምናለን::

በተጨማሪ ጥላሁን ታከለ የአንድ ሰውን ስም የሚ
ወክል ስም መሆኑ ግልጽ ከመሆኑም በላይ አባሎ
ቻችን በጥቅልም ሆነ በነጠላ በጽሑፍም ሆነ በቃል
"ጥላሁን ታከለ እኛ ነን" የሚል መግለጫ አው
ጥተው አያውቁም:: ስለዚህ ሸቪኒስቶችና አድሀሪዎች
ሁሉ ሁላችንን በጠቅላይ መጥቀስ ቀርቶ ከአባሎቻችን
ማንኛውንም በጥላሁን ታከለ ስም የሚወቅሱበት ምን
ምክንያትና ምን ህጋዊ ማስረጃ እንዳላቸው ለማወቅ
አልቻልንም:: ነገር ግን የሰናይ ልቤ ቶናው ፀረ
ረቮሉሽናዊ ተግባር እኛን በጥላሁን ታከለ ስም መዝ
ለፍ አይደለም ቶናው ስራ "ምስጢራዊ ድርጅት"
የሚያነብ የገል (ምናልባት የምስጢራዊ) ደብዳቤ ሰርቆ
በዚሁ መጽሔት ለአድሀሪው መንግሥትና ለአሜሪካ የስ
ላይ ድርጅት ጥቅም አትሞ ማውጣቱ ነው:: ሰናይ
ኦስቦ ይሥራው አይሥራው ይህ የሰላይ ሥራ ብቻ ነው::
ደብዳቤው የሚጠቅሰው "ምስጢራዊ ድርጅት" ካለ
የሚቃወመው ፊውዳሊዝምና ኢፔሪያሊዝምን (ቢያንስ ቢያ
ንስ የኃይለ ሥላሴን መንግሥት) መሆኑን መንም የኢት
ዮጵያን የፖለቲካ ሁኔታ የሚያውቅ ሰው ያውቀዋል::
ስለዚህ ገና ለገና ደብዳቤውን ጽፈዋል ብሎ የሚጠረ
ጥራቸው ሰዎች በጥላሁን ታከለ ስም በርዕሶቱ ዓለም
የተቃወሙት የኢትዮጵያ "የግራ ክንፍ" ተማሪዎች



ናቸው ብሎ አያመን ስለነሱ ድርጅታዊ ምስጢር አትሞ
ማውጣት ማንን ይጠቅማል? ጥላሁን ታከለ በብሔሮች
ጉዳይ ላይ ያቀረበውን ክርክር ማፍረሽ መቼም ሲሆን
አይችልም! ዓላማው ምንድነው?

እዚህ ላይ መገለጽ ያለባቸው ነገሮች አሉ::

1ኛ) ማህበራችን የተባለውን ደብዳቤ ፈጽሞ አልጻፈም::
2ኛ) ማህበራችን ከመቋቋሙ በፊት አባሎቻችን ደብዳ
ቤውን በጥቅልና በጋራ በስማቸው አልጻፉም:: በተረፈ
አባሎቻችን ለግለሰብነት በሚጽፉት ደብዳቤ ሁሉም በጠ
ቅላይ ኃላፊነት በለማይወስዱ፣ ግለሰቦች በሚጽፉት
ደብዳቤ የሚያገባቸው ነገር የለም:: ስለዚህ ደብዳ
ቤው በማህበራችን ስም ወይንም በቡድን ስም ያልተጻፈ
መሆኑንና ምንም ኃላፊነት እንደሌለን ከመግለጽ በስተ
ቀር ሌላ የምንጠየቅበት ጉዳይ የለም:: የግለሰብ
አባሎቻችንን ደብዳቤ የምንከታተልበት ሀይልና መብት
ቀርቶ ምንም ምክንያት የለንም፣ እንደሰናይ ልቤ
የኢትዮጵያ ተማሪዎች የቅርብ ጓደኞቻቸውና ጓደኞቻቸው
የሚጽፉትን የሆነና ያልሆነ ወሬ ለማወቅ ደብዳቤ
የምንበረቅበት ምክንያትና መብት የለንም:: ስለዚህ
የተባለው ደብዳቤ ከማህበሮቻችን አባሎች በአንዱ
መጻፉን እንኳን ብናውቅ የተባለውን ደብዳቤ በማጻፉ
በመሰረቱ ( in principle ) የምንወቅስበት

ምክንያት የለንም፡፡ ማንም ሰው ለቅርብ ጓደኛውና
ጓዱ እንደለቡ፣ ሰይወጣ ሰይወርድ፣ የሆነ ያልሆነ
ነገር፣ ሐሜት፣ ያልተረጋገጠ ወሬ፣ እንደሚሸፍ
ማንም አያውቅምን (በናይ ራሱ ለቅርብ ጓደኞቹ
ስንት ነገር መጻፉ እንደማይቀር ዓለም አያውቀው
እዚህ ላይ ወቀብ ማቀረብ ቀጥ የሌለው አጭበርበ
ሪነትና ሰበብ ፍለጋ ነው) ነገር ግን በደብዳቤው
ላይ ስለተጠቀሰው ድርጅት ማህበራችን ሆነ የማህ
በራችን አባሎች የሚያውቁት ነገር እንደሌለ መግ
ለጽ እንፈልጋለን፡፡ ያም ሆነ ይህ፣ እንዲህ ያለ
ድርጅት ቢኖር ኖሮ ቢ አይ ኤና የኃይለ ሥላሴ
ፀጥታ የበናይን መሸሸጊያ ይዞ መከታተሉና እስከ
ዛሬም ማፍረሱ አይቀርም ነበር፣ ወይንም ድር
ጅት መኖሩን በተግባሩ ባወቅን ነበር፡፡

ዋናው ፍሬ ነገር በናይ ልቢ ህግ ወጥ በሆነ
መንገዱ አሳግባብ እኛን ከመወንጀሉም በላይ እው
ቀውም አሳውቀውም፣ የረቮሉሽን ገብረ ገብነት
የተለየው ጠርቦ ፀረ ረቮሉሽናዊ ተግባር መሠረቱ
ነው፡፡ የሉንዱ ጓደኞች በሚያዝያው "ታጠቅ"
በወጣው ጥናታቸው ላይ ስንት ጥያቄን የተማሪ
"ጉዳለት" ሲዘረዝሩ ይህንን ወደር የሌለው ፀረ
ረቮሉሽናዊ ተግባር (ደብዳቤውን እኛ የጻፍነው
ቢመስላቸው እንኳ ልዩነት አያመጣም) ጠርሰው



በያነሱ በመጽሔቱ ያገኙት ጥፋት ጓደኞችን "ልጆች"
ብሎ የሚሰደብ ሐረግ መሆኑ ብቻ አይደለም፡፡
መጽሔቱ "ለጠላት መሣሪያ" መሆኑን ቢገልጹም
"ጥፋተኞች" በሏቸው ሰዎች "እንደ አጋጣሚ"
ሁሉም በበሔሮች ጉዳይ ላይ አንድ አቋም የገለጹ
ነበሩ፡፡ ላይ ያቀረቡትን ዘለፋና የተጋነነ ሂስ
ዕውነት ለማስመሰል ያተቱትን ያህል ስለሰናይ ተግባር
መጻፍ ቀርቶ "ለጠላት መሣሪያ" ሆኗል ላሉት
እንኳን አንዱም ምክንያት አለመስጠታቸው አይገርመንም፡
በአንዱ በኩል ሰይጠቅሱት ካለፉ ሐቀኛው ተማሪ
ጠርቦ የጥናታቸውን ዓላማ እንደመጠርጠር በማወቅ ያፈሩ
በሌላ በኩል በግልጽ ያነን ፀረ ረቮሉሽናዊ ተግባር
ገልጸው መጻፉ እነሰናይን ጠርቦ የሚያጋልጣቸውና አዱ
ሃሪ መልካቸውን የሚያሳይ እንዳይሆንባቸው ያፈሩ
ይመስላል፡፡ ይህ ድርጊታቸው ከመሰረታዊ አቋማቸው
የመነጨ ነው፡፡

ለ) ፀረ ረቮሉሽናዊ የፈቶዓል "ገብረ ገብነት"
በግራ ክንፍ ህሊና ላይ ትልቅ ተፅዕኖ ያለው
መሆኑን ወለል አድርጎ ያሰየን ከላይ የጠቀ
ስነው ጉዳይ ባይሆን በዚያ የአጭበርበሪያችና
የሰላዮች "ቻሌንጅ" መውጣት ምክንያት

በኢ.ኪ.ተ.ማ ፕሬዝዳንት በአልሁ ፈለቀና በዚሁ ቀደም "የቻሌንጅ" አዘጋጅ በነበረው በመለሰ አያሌው መሃከል የተፈጠረው ጠብ ነው። እስካ ሁን ያነበብነው ሁለቱም የጻፏቸው ግልጽ ደብዳ ቤዎችና በትግላችን ላይ ስለዚሁ መጽሔት የወጣ ውን መግለጫ ብቻ ነው። ስለ አጭበርባሪው መጽ ሔት እውነተኛ ደራሲዎችና በሁለቱም መካከል ስላ ለው ግኑኝነት የምናውቀው ነገር ስለሌለ የጓዴ አልሁን በደል ልክ አሁን መናገር አንችልም። ሆኖም የመለሰ አያሌውን ግልጽ ደብዳቤ ስናነብ ለኢትዮጵያ ተራማጆች ነበረ ገብነት የተሰማንን ሀፍረትና ድንጋጤ መግለጽ እንፈልጋለን።

መለሰ አያሌው፣ አልሁ ፈለቀና የቅርብ ጓዶች "የቢዛንታይን ፖለቲካ" (ምንም ነበረ ገብ ነት የሌለው የተንኮልና የሴራ ፖለቲካ) ፈጸሙ ብኝ በማለት የዘረዘራቸውን መረጃዎች በተራማጅ ጓዶች ይፈጽማሉ ብለን ማመን አቅቶን ሌላ ማስ ረጃ እስክናገኝ ዝም ብለን ነበር። አሁን ግን ጓዴ አልሁ ምንም ዓይነት የማስተባበያ መግለጫ ወይም የግለ ሂስ ጽሑፍ ስላላወጣ አስተያየታች ንን መግለጽ የግዴ ይሆንብናል።



በመጀመሪያ የጉዳዩን ዝርዝር በደንብ ለማ ያውቁት ወይም ለረሱት ጓዶች አንዳንድ ነገሮችን እናስታውሳለን። በአሜሪካ የኢት ዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መጽሔት በ"ቻሌንጅ" ስም አምና በነሐሴ ወር አንድ መጽሔት ወጣ። የመጽሔቱ ፎቶ ኮፒ ተልኮልን እንዳየነው የመ ጽሔቱ ቅርጹና የታተመበት ማተሚያ ቀደም ብለው ከወጡት የ"ቻሌንጅ" መጽሔቶች የማይለይ ከመሆኑም በላይ በአዘጋጅ ስም እስከዛን ጊዜ ድረስ የ"ቻሌንጅ" አዘጋጅ የነበረውን የመለሰ አያሌውን ስም ይዟል። በመጽሔቱ ውስጥ ያሉትን ጽሑፎች በጥብቅ ያልመረመረ ሰው ወይም የመለሰ አያሌውንና በአሜሪካ ያሉ ትን የኢትዮጵያን የግራ ክንፍ ተማሪዎች የፖ ለቲካ አስተሳሰብ የማያውቅ ሰው፣ መጽሔቱ እውነተኛ አለመሆኑን መገመት ያዳግተዋል። በመጽሔቱ ውስጥ ያሌትን ጽሑፎች ልብ ብሎ ያነበበ ሰው፣ ጽሑፎች ውስጥ ያሉትን የፖለ ቲካ ሐሳቦች (በተለይም የሶቭየት ሕብረትን ፕሮፖጋንዳ) ከዚያ በፊት መለሰ አያሌውም ሆነ ሌሎች የግራ ክንፍ ሰዎች እና እስከ ምናውቀው ድረስ በይፋ ደግፈዋቸው አያውቁም፤

እንደዚያ ዓይነት አስተሳሰብ ያላቸው መሆኑንም ከዚህ በፊት ሰምተን አናውቅም:: የሶቭየት ህብረትን የፕሮፓጋንዳ (በተለይም ፀረ ቻይና የሆነውን ክፍል) የሚደግፍ እንዲሁም የግራ ክንፍ ኢትዮጵያዊ መኖሩን ሰምተን አናውቅም:: ይኸንን ያህል የሚያውቅ ሰው መጽሔትን ያወጣው ሰው (መለስ አያሌው ይሁን ሌላ ሰው) ያንን የተጠቀሰውን ሐሳብ <u>በግልጽ</u> የማይደግፍ እንደ ሆነና መለስ ቢያትመው እንኳ አላተምኩም እንደሚል ግልጽ ይሆንለታል:: ስለዚህ የመጀመሪያው ጥያቄ መሆን ያለበት <u>አዘጋጁ ማንም ይሁን ማን</u> መጽሔትን ሲያወጣ <u>ዓላማው ምንድን ነው?</u> የሚለው ጥያቄ ነው:: ፀረ ሶቭየት ጥላቻ ዓይኑን የሸፈ ነው፤ ስለ አድሃሪ መንግሥታት የበላይ ድርጅቶች ያሠራር ዘዴ ምንም አይነት ሀሳብ የሌለው ሰው ካልሆነ በስተቀር:: "<u>የመጽሔቱ ዓላማ የሶቭየት ህብረትን ፕሮፓጋንዳ ለማስፋፋት ነው</u>" የሚል የለም:: ምክንያቱም አዘጋጁ የተባለው ሰው ተነስቶ በመጽሔቱ የገለጹትን የሶቭየት ህብረትን ፕሮፓጋንዳ የሚቃወም መግለጫ ቢያወጣና እነዚያንም ጽሑፎች የሚደግፉቸው ተማሪ ቢጠፉ ይኸንኑ ፕሮፓጋንዳ ያነበበ ሰው መቀበሉ ቀርቶ



በይፋ ኖሮ ከሚኖረው ጥላቻ የበለጠ ጥላቻ እንደሚያሳድር ግልጽ ስለሆነ ነው:: የኢትዮጵያ ተማሪ የሶቭየት ህብረትን ፕሮፓጋንዳ የማይደግፈው በዚህ በአጭበርባሪ ቻሌንጅ የወጡትን የመሳሰሉ ጽሑፎች ስላላነበበ አይደለም:: ስለዚህ ዓላማው የሶቭየት ህብረትን ፕሮፓጋንዳ ለማስፋፋት ወይም የኢ.ተ.ማ.በአ(ESUNA) አስተሳሰብ ለማስመሰል እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: ምናልባት ኢ.ተ.ማ.በአ ወይም መለስ አያሌው በቁጣ በሶቭየት ህብረት ሳይ ዘለፉ ወይም ወቀሰ እንዲያወጡ ፈልጎም ይሆናል::

የመጽሔቱ ዓላማ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ውስጥ ፍጹም መጠራጠርን ለመፍጠር ነው:: 1ኛ) ጽሑፉን ያዘጋጀው መለስ አያሌው ነው ከተባለና ቢከዱ ተማሪው ካላመነው ከዚያ ቀጥሎ ማንኛውም ተራማጅ ኢትዮጵያዊ በይፋ የሚናገረውን የፖለቲካ አቋም "ከልቡ አያምንበትም" የሚል ጥርጣሬ እንዲስፋፋ ፈልጓል:: 2ኛ) መለስ አያሌው በሚከዱበት ጊዜ "ደራሲው ማነው" ሲባል ተማሪዎች (በተለይ በበሶርች ጉዳይ ላይ ለሁለት የተከፈሉት) እርስበርሳቸው እንዲጠራጠሩና በመሃከላቸው ፍጹም መተማመን እንዳይኖር ነው በሁሉቱም በኩል የአዘጋጁ ዓላማ በኢትዮጵያ ተማሪዎች መካከል ፈጽሞ መተማመን እንዲጠፋና መወነጃጀል

ተሰራፍተ ምናልባት እንዲደባደቡ ...ወዘተ
በዚህም ምክንያት የተማሪ ማህበራት እንዲፈ
ርሱ ነው:: የዚህ አይነቱ ዓላማ ሲኖረው የሚ
ችል የአድሀሪው መንግሥት ፀጥታ፣ ሲ.አይ.ኤ
ወይም ሌላ የኢትዮጵያን ተማሪዎች ማህበራት አን
ደጠላት የሚያይ ድርጅትና መንግሥት ገለ ሰብ ነው
ተማሪ በዚሁ ተግባር ላይ ከተከፈለ የነዚሁ ድር
ጅቶች ወኪል (ሰላይ) ወይም ጠርብ አእምሮ—ጠባብ
የሆነና ጠላት መሣሪያ ሲያደርገው የማያውቅ ተማሪ
ነው:: ስለዚህ ነው ምንም በርዕዮተ ዓለሙና በፖለ
ቲካ አስተሳሰቡ በንፃወሙ <u>መሰስ አያሌው የተማሪውን
ማህበር ጠርቦ ሲያጠሩ ይፈልጋል ወይም እንዲህ ያለ
የስላይ ሥራ ይሰራል ብለን መጠርጠር ያልቻልነው</u>::

መጽሔቱ የአድሀሪ መንግሥት የስላይ ድርጅት ሥራ
ነው የሚለውን ሐሳብ ያጠነከረው፤ የስላይ ድርጅ
ቶች በጠላቶቻቸው መንግሥታትና ድርጅቶች ላይ
"የሳይኮሎጂካል ጦርነት" በሚል ስም የሚያሰ
ራሩት የፕሮፓጋንዳ ዘዴዎች ስለአሉበት ነው ቀናው
አላማቸው በህዝቡ መካከል ጥርጣሬንና ማወናበድን
ለማስከተል ሲሆን በነዚሁ መንግሥታትና ድርጅቶች
በደረናው ደጋፊና አቀጋሽ የሚመስል ጽሑፍ ጽፎ



አንባቢው ልብ ሊል በህሊናው እንዲቀረፅ የሚፈ
ልጋቸውን "እውነቶች" አለፍ አለፍ ብለው በጽ
ሑፎች ውስጥ ጣል ጣል ማድረግ ነው:: ከሶቭየት
ህብረት ፕሮፓጋንዳ ጽሑፎች ሌላ በመጽሔቱም የታተ
ሙት ጽሑፎች ዓላማ በሙሉ ይኸው ነው::

ሀ) ርእስ አንቀጹ "የኢትዮጵያን ሬቮሉሽን የሚመ
ሩት ተማሪዎች መሆን አለባቸው" የሚል ሐሳብ
ይዟል::

ለ) ስለ ኤርትራ የተጻፈው፤ የኤርትራን ትግል የሚ
ደግፍ መስሎ አንዱ ቦታ "በኤርትራ ትግል
ታሪክ በስላይነት የተያዙት ሁሉም ክርስቲያኖች
ነበሩ" የሚል የሐሰት ወሬ ጣል ያደርጋል፤
ሌላ ቦታ ደግሞ "ህዝቡ ጂሃድ ካለ እኛም
ጂሃድ እንላለን" ይላል:: የዚህ ዓይነት፤
ቁጥር ስፍር የሌለው የኤርትራን ህዝቦች
ትግል ታሪክና ጊዜአዊ ሁኔታ የሚያጣምም ብዙ
"ወሬ" አለበት:: ሌላው ትልቅ ወሬ ግን
"የሚቀጥለው ምክንያታዊ እርምጃ" ("THE NEXT
LOGICAL STEP") በሚል እርእስት
በተጻፈ ዝብዝንኬ ጽሑፍ ውስጥ ጣል የሚያደ
ርገው ነው:: "የመጀመርያው በተማሪ የሚመራ
የህዝቦች ተዋጊ ቡድን ሥራውን ትግሬ ጠ/ግዛት

ጀምሬል፤ የትግራይ ትግርኚ ነፃ አውጪ ግንባር በፀጥታ ኃይሎች ላይ አደጋ ይጥልና ገጠር ገብቶ ይጠራል ...፡ ይላል፡፡ ከአምና ነሐሴ በፊትም ሆነ በኋላ እንኳንስ በተማሪ የሚመራ " ተቃጊ ቡድን " ይቅርና ምንም አይነት የጦር ትግል ቡድን ትግሬ ጠ ግዛት ውስጥ ውጊያ መጀመሩን አልሰማንም፤ አልነበረም፤ የለም፡፡ ስለዚህ ወሬው የሀሰት ወሬ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህ " ወሬ " የተጻፈበትም ምክንያትና ዓላማ ግልጽ ነው፡፡ ከዚያ በፊት አንዳንዱ አዕምሮ ጠባብ ሾቪኒስቶች በኛ ላይ "የብሔሮችን መብት፤ በተለይ የኤርትራ ህዝብን የመገንጠል መብት የደገፉት በኤርትራ በኩል ገብተው ትግሬ ሲዋጉ ስለፈለጉ ነው ፡..ወዘተ "እያሉ በሰፊው ያሰወሩትን፤ መሰረተ ቢስ የፈቀዳል ተንኮል የተማሰበትና ወሬ መሰረት በማድረግ በተማሪው መሃል (በተለይም በትግሬዎችና በሌሎች መሃከል) ቀርጤረ ለመፍጠር ነው፡፡ መጽሔቱን ልብ ብሎ ሳነበበው ሰው ተማሪዎች የሶቭየት ፕሮፓጋንዳ ይደግፋሉ ለማስኘት ከተጻፉት ጽሑፎች ይልቅ በሌሎች ጽሑፎች ላይ የተጠቀሱት ነገሮች የበለጠ አባባችና ለተማሪው እንቅስቃሴም አንድነትና እድገት አደገኛ መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡



ጓዱ እልሁና ሌሎች የአ ኢ ተ ማ መሪዎችና የ " ትግላችን " አዘጋጆች ግን ያናደዳቸው የአሜሪካው ማህበር የሶቭየት ህብረት ፕሮፖጋንዳ " ደጋፊ " መባሉ ነበር፡፡ ስለዚህም በ" ትግላችን " (ጥቅምት 1964 ዓ.ም) ይሆኑ የሶቭየት ፕሮፖጋንዳ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንደማይደግፉ ገልጸው "አዘጋጁ" የተባለው መለስ አያሌው " መግለጫ " እንዲሰጥ ጠይቀዋል፡፡ ጓዱ እልሁማ ከዚህ ሁሉ አልፎ ተርፎ "ያነሳሳህን እውነተኛ ዓላማህን" (" motive ") ግለጽ ቢል ለመለስ አያሌው ግልጽ ደብዳቤ ጽፎለታል፡፡

መለስ አያሌው የጻፈውን ምረት ያለበትን የ "ቅርርጥ" ደብዳቤ ሲጽፍ የዘረዘረው ጉዱ ስለ ኢትዮጵያ የግራ ክንፍ ተማሪዎች የነበረንን አስተሳሰብ አናገቶ ረጋ ብለን በሰፊው እንድናስብ ገፋፍቶናል፡፡ የጉባዔው ተካፋዮች በሙሉ ያንን ደብዳቤ እንደገና ቢያነቡት ደስ ባለን፡፡ ነገር ግን እዚህ አንዳንዱ ነገር እንጥቀስ፡፡ የእልሁ ደብዳቤ የተጻፈው በኦክቶበር 13/71 ሲሆን የመለስ አያሌው ደብዳቤ የተፃፈው ደግሞ በኦክቶበር 23/71 ነው፡፡ መለስ መልሱ ከመጻፉ በፊት

"ትገሳችን" ላይ "መገሰጫ" ስጥ የሚል ጽሑፍ ወጥቶ ነበር:: መለስ አልሁን "ቢዘንታ ይን ፖለቲካ" ትበራለህ ብሎ ለማውገዝ የሰጠው ቀና ምክንያት የ"ትገሳችን" ጽሑፍና የአልሁ ደብዳቤ ከመጻፉ በፊት ለዓለም አቀፍ መሪዎች የአ.ኢ.ተ.ማ መሪዎች ለመጽሔቶች መሪዎችና ለራሱ ለአልሁ መለስ ያንን መጽሔት ፈጽሞ እንዳልጻፈ የገለጸላቸውና የተቀበሉት መሆኑን በግል ደብዳቤ ዎች ከገለጹለት በኋላ <u>በጉን</u> <u>በይፋ</u> በወጡት መግለ ጫና በግልጽ ደብዳቤው ላይ 'ስለንባቡ ዕውነተኛ ዓላማ' እንዲያስረዳ መጠየቃቸው ነው:: መለስ እንደሚለው አልሁ ደብዳቤውን ከመጻፉ በፊት የሱን አቋም ያውቅ ነበር::

ሀ) በመስከረም መጀመርያ ላይ 'አውሮፖ ካሉት ጓደኞችህ አንዱ ስለመጽሔቱ ጠይቆኝ አልጻፍ ኩም ብቀቀለሁ ይላል::

ለ) "በሁለት ሣምንታት በኋላ" ስቂዱን ካላችሁት ከጓደኞችሁ "ከሚለው ሰው ሌላ ደብዳቤ" እንደደረሰው ገልጾ ለዚሁ ስቂዱን ላለው ሰውና መጀመሪያ ለጻፈለት ሰው የአሜሪካኑ ማህበር ይህንኑ አጭበርባሪ ቻሲንጅ አለመጻፉን ካልገ ለጸ በኢትዮጵያ ተራማጆች መሃከል የሚፈጠረው



መወናበዱ አደገኛ እንደሚሆን ገልፀንላቸው ነበር ይላል::

ሐ) ነገር ግን ከነዚህ ደብዳቤዎችም በኋላ "እኛ የጻፍነው መሆኑን ያመናችሁ ለመም ስል ፈለጋችሁ ካለ በኋላ" በ "ትገሳችን" ላይ ለመጽሔቱ ሥራ "የመጀመርያዎቹ ተጠርጣ ሪዎች እኛ መሆናችንን አስታወቃችሁ" ይላል።

መ) በኦክቶበር 1 3 5 15 ላይ የአልሁ ቅርብ ጓደኞች ናቸው ከሚላቸው ሁለት ሰዎች ይሸው "ቻሲንጅ" በአጭበርባሪዎች የታተመና እነሡ ለስም እንዳልሰሩት የሚያምኑ መሆናቸውን ገልጸው የጻፉለትን ደብዳቤዎች ጠቅሶ ይጽፋል::

መለስ እንደሚለው በ "ትገሳችን" መገሰጫ አውጪ ብለው የጻፉት ሰዎችና "ዕሁነተኛ ዓላማህን ግለጽ" ያለው አልሁም የጻፉትን ነገር ከመግለጻቸው በፊት መጽሔቱን እነሱ አልጻፉትም ብለው እንደሚያምኑ ቀደም ብለው በግል ደብዳቤ (ቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ) ገልጸውለት ከሆነ በ"ትገሳችን" የወጣው ጽሑፍና የአልሁ ደብዳቤ የመጠረሸ ወራዳ ሥራና የፊውዳል ቤሬ ነው:: ሌላ ስም ሊሰጠው አይቻልም::

እነርሱ "አልጻፍኩትም" እያሉ ከገለጹላቸው በኋላ ወይም አልጻፍኩም ማለቱን ከሰሙ በኋላ፣ ስንት ሰው በሚያነበው በ"ትግላችን" ላይና በግልጽ ደብዳቤ ላይ መከፋትን በምንም መንገድ ሳይገልጹ "መግለጫ ስጥ" ያነሳሳህን ዕውነተኛ ዓላማ (motive) ግለጽ" ብሎ መጻፍ ዓላማው ፈጽሞ ሊገባን አይችልም:: አይጠረጠሩ፣ ልንል አንችልም፤ ነገር ግን ያንን የወረዳና የበላይ ሥራ ይሰራዋል ብሎ መጠርጠር ቀላል ነገር አይደለም:: በተለይ ስንት ዓመት የሚያውቁትን ምናልባት "ጓዴ" እያሉ ይጠሩት የነበረውን ሰው (ስም ሳይገለጽ ከአውሮፖና ከሰሜን ጻፉልኝ የሚላቸው ሰዎች ለብዙ ጊዜ ያውቁት የነበሩ እንደሱ የተማሪ መሪ የነበሩ ናቸው ብለን ብንገምት የምንሳሳት አይመስለንም) የተጨበጠ ማስረጃ ሳይዙ መጠርጠር ከባድ ነገር ይመስለናል:: በርዕዮተ ዓለም መለያየት መጣላት አንዱ ነገር ነው:: ስንት ዓመት "ጓዴ" እያሉ ሲጠሩት የነበረን በግልጽ "የግራ ክንፍ" ወገን ሆኖ (መሪ ሆኖ) ለብዙ ዓመታት የታወቀን ሰው፣ በላይ የሚሠራውን ተግባር ይሰራል ብሎ መጠርጠር ሌላ ነገር ነው:: ዋናው ያደናገጠን ነገር በእነዚህ የግራ ክንፍ ጓዶች መሃል ያለው "ጓዴነት" እንኳንስ የጠላት ቀይት፣ ተራ የበላይ የመለያያ ተንኮል የሚበታትነው፣ ለእንገት በላይና



ጊዜያዊ የሆነ መቀራረብ እንጂ እውነተኛ በጋራ የላብ አደር ርዕዮተ ዓለምና የጋራ በሆነ ረቮሉሽነሪ ቆራጥነት ያልተሳሰረ የይስሙላ "ጓዴነት" መምሰሉ ነው:: በዚህ ግምታችን የተሳሳትን ሆነን እንድንገኝ ሙሉ ምኞታችን ነው::

ነገር ግን ያንን የበላይ ሥራ "አልሠራሁም ብሏል" ብሎ በ"ትግላችን"ላይ ለመጥቀስ ያህል መልስ እያለው አልሰራውም ብሎ ማመን የሚያስፈልግ አይመስለንም:: በተለይ መጽሔቱን ያወገዙት የሶቪየት ህብረትን ፕሮፖጋንዳ ከያዙት ሁለት ጽሑፎች ውስጥ ከሰፈሩት ሀሳቦች በአብዛኛዎቹ ስለማይስማሙ ከሆነ፣ መልስ እያለው የሶቪየት ህብረትን ፕሮፖጋንዳ ስለ "ደገፈ" ጠርሶ ከኃይለ ሥላሴና ከኒክሰን ጎን የተሰለፈ የመደብ ጠላት መሆኑ ነውን? በተለይ እሱ የጻፈው መሆኑን የሚያሳዩበት ማስረጃ ሳይኖራቸው፣ በይሆን በይሆን "እኔ አልጻፍኩም" ብሏል፣ እኛ ግን አላመንነውም" ማለት ያበት አይደለም? መልስ እንደሚለውማ "እንተ እንዳልጻፍከው እናምናለን" ብለውት ከሆነ፣ ከዚህ የባሰ ወረዳ ተንኮል ከዚህ የተሻለ የፊውዳል ርዕዮተ ዓለምንና የፊውዳል የፖለቲካ ትግል ዘዴን የሚገልጽ ተግባር የት ይገኛል? የለም፣ ጓዶች፣ የሰርቶ አደሩ ረቮሉሽን ቀርቶ የቡርዧ ዲሞክራቲክ ረቮሉሽን እንኳን በዚህ ዓይነት መንገዱ

አይበገም! እንዲህ ዓይነቱ፣ ከላብ አደሩ ገበሬ ግብነት የራቀ ዘዴ የተሸለ ህብረሰብና'' ከፍተኛ ጭን ሰው'' ለማምጣት የሚሆን አይደለም።። ''ጓደኛ'' እየተባበሉ በአንዱ አኛቸው አንገት ሳንገት ተያይ ዘው እየተባበሙ በሌላው አኛቸው በየአርስ በርስ ቸው ጀርብ ሳይ ጩቤ የሚሰኩት የፊዩዳል መስፍንት ናቸው።።

በኛ አስተሳሰብ፣ የዚህ ዓይነት ተግባር በተማሪ መሃከል አለመተማመንን ፈጥሮ መለያየትን ያስከትላል እንጂ በአደባባይ የተገለጸ የፖለቲካ አቋምን ተርጉሞ "ሸቪኒስት'' ብሎ መበየም መለያየትን አይፈጥርም።። መልስ፣ የተባለው አቋም ሸቪኒስት አቋም አለመሆኑን ማሳየት ነው! የስላይ ሥራ ትሰራለህ ብሎ መጠርጠር ወይም <u>በተደበቀ ሥራ</u> ተከፋፍለህ ማለት ግን መልሱ የመጨረሻ መቆራረጥ ነው፣ በተለይ ጓዶች በሚባሉ መካከል ቢሆን <u>የሎንዶ ጓዶች በዚህ ወራዳ ተግባር ላይ በሚያዝያው '' ዝነኛ '' ሂባቸው አንዲት ያል አልተናገሩም</u>።። ምነው የጓዶች መቆራረጥ የተማሪውን ማህበር አይከፋፍልምን? ወይስ የኢትዮጵያን ሬቮሉሽን ይጠቀማል ብለው ያምናሉ!



2ኛ) <u>የፊዩዳል ርዕዮተ ዓለም በጓዶች ሀሳና ያለው ተፅዕኖ በፍልስፍናና በህብረ ሰበዊ ሀሳቦቻቸው</u> ( Social ideas - Social values ) <u>ላይ ይታያል</u>።። አንዳንዱ ጓዶች ስለሰበው '' ክብር '' በለ''ዕውቀት'' በጓዶች መሃከል ስለሚገኘው ግኙኘነት ጠባይ ያላቸው አስተሳሰብ ያው የፊዩዳል አስተሳሰብ ነው።።

ሀ) ቀላሁን ታከለ አነሴቶስን '' በሸል ሸቪኒስት'' በማለቱ አንዳንዱ ጓዶች ሂስ አቀርበው ነበር።። እነዚህ ጓዶች አነሴቶስ '' ቦሸል ሸቪኒስት'' መባላቸው ትክክል መሆኑንና በብሔሮች ጉዳይ ላይ የጠበቁት አቋም '' የቦሸል ሸቪኒስት'' አቋም መሆኑን ''ቦሸል ሸቪኒስት'' የተባለው ስያሜ ትክክለኛ ሰያሜ መሆኑን ያምኑና፤ '' በቻ አጠራሩ ጠንካራ ስለሆነ በዚያው አቋማቸው እንዲረጉ ያደርጋቸዋል'' ይላሉ።። የሚቀርበው ምክንያት ገሰጽ ነው።። ''ክብራቸው'' የተነካና ''የተቀረቱ'' ስለሚመስላቸው በጭም ተቀረቱ ስለሚል ነው።። ይህ የፊዩዳል አስተሳሰብ ነው።። በፊዩዳል አስተሳሰብ እንዱ ሰው '' ዐዋቂ'' የሚባለው በደፈናው በለሆነ ሁሉን ነገር የሚያውቅ ያስመስላል።። በለዚህ በምንም ነገር (ተራም ነገር ቢሆን) ዐዋቂ አለመሆኑ በህዝብ ፊት፣

በአደባባይ በታየ ጨቀሳሳ ዕውቀቱ የተሸረ ይመስል ተቀረደ ማለት ነው፡፡ መጀመርያ እንዴ ሰው ሁሉን ነገር አለማወቁ ምንም ነውር እንደሌለበት፣ ዐዋቂ አይደለም ቢባልም ምንም ነገር እንደሌለበት ሙሉ በሙሉ ያልተቀበሉ ጓደኞች አሉ፡፡ ቢሆንም ጓደኞች እን ዳሉት፣ እነሆንስ "በዘራቸው እንዳይቀነስ" በበሌ ሮች ጉዳይ ላይ የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እንኳን እንዳልተባበሩና በርዕዮተ ዓለሙ ትግል ጊዜ የተን ባውን ክርክር ቀደም ብለው እንደሚያውቁት፣ ሊያስ ምትን ይቆክራሉ፡፡ ከዚህ አልፈው ተርፈው እነሡና ይማ አቋማቸውን መቀየራቸውን ማመን ቀርቶ፣ ቢያንስ ቢያ ንስ "አገም ደገም" እንዳያደርጉት እንኳ ጠርሰው አያምኑም፡፡ ከናካቴው፣ "<u>በመገንጠል ሀሳብ ላይ የተነሳ ማንኛውም እንቅስቃሴ ፀረ—ረቮሉሽናዊና ስኢ ትዮጵያ ረቮሉሽን ጉዲ ነው</u>" የሚለውን የአሜሪካውን ማህበር የ1969 አቋም "<u>የብሔሮችን የመገንጠል መብት አንደግፋለን ነን</u>"...ከሚለው ከሁኑ አቋማ ቸው ጋር አንዱ እንደሆነና የ1969 አቋም ስህተት እንዳልነበረ፣ እየማሉ እየተገዘቱ ዓይን በይን ሊያ ታልሉን ይቆክራሉ፡፡ ይህ ሁሉ የፊውዳል ርዕዮተ ዓለም ስለ "<u>ክብር</u>" ስለ "<u>ውርደት</u>" በህሊናቸው ውስጥ የቀረፀው አበተባሰበ መግለጫ ነው እንዴት



ተደርጉ! "ዐዋቂዎች" ትንሽ እንኳን ተሳስተው ነበር ከተባለ ሰማይ መረቱ ተገለባበጠባቸው ማለት ነው! በዚህ ዓይነት ለወደፊቱም ረቮሉሽኑ ሲጀመር ተሳስተው ፀረ ረቮሉሽናዊ አቋም ቢይዙና አቋማቸው ፀረ ረቮሉ ሽናዊ ነው ቢባሉ ፀረ ረቮሉሽናዊ እንደሆኑ ይቀራሉ ማለት ነው!

ለ) የፊውዳል ፍልስፍና <u>የዕውቀትንና የፀጋን</u> ( virtue ) <u>መጠን</u> የሚለካበት መሣሪያ እንደ ገለብ በሚሰራው ሳይሆን <u>በእድሜው</u> ነው፡፡ እንዲያውም በአማርኛ ፀዋቂ የሚለው ቃል ሁለት ትርጉም አለው፤ አንዱ፣ በዕድሜ የበሰለ (ልጅነቱን የጠረሰ) ማለት ሲሆን፣ ሌላው ዕው ቀት ያለው ብልህ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የሁለት በያ ችን ዕውቀት ለመመዘን መጀመሪያ የሚታየው ዕድሜአቸው ነው፡፡ ጥሳሁን ታከለ ሂስ ያቀረበባቸው ሰዎች የጸ ሐፊ "ደራሲ ዎች" አለማስረጃ እና መሆናችንን ስላ መኑ፣ የኛም ዕድሜና አገር ውስጥ የነበርንበት የትም ህርት ደረጃ የታወቀ ስለሆነ ከኛ ቀረብ ብለው የሚያ ምኑትን ሂስ መቀበል የ"ውርደት" መጠረጃ መስሎ ታያ ቸው፡፡ ስለዚህም ሐጉስ በኛ ላይ ሊሰነዝረው የቻለው ትልቁ የማጣሪያ ስድብ "አልጄርያ ያሉት ልጆች" (" the boys in Algeria ") የሚለው ነው! "ስድብ" ብሉ የሚነገን ትርጉም የሌለው ስያሜ፣

ምንም በይበማንም ዐላማው እኛን "ዐዋቂ ያልሆኑ"፣
ገና "ያልበሰሉ" ብዙ ያላዩ ያልለዩ ለመስደብ መሆ
ኑን ስናውቅ በዕውነት ከት ብለን ለመሳቅ በስተቀር
ሌላ ልናደርግ አንችልም። ሐጐስ፣ ይህ የሱ ስድብ
ኢትዮጵያ ያሉትን የግራ ክንፍ ተማሪዎች ቀርቶ፣ በመ
ቀሳሳው የወጡትን ትውልድ አስተሳሰብ የሚያስቅ እንደ
የሚያበሳጭ መሆኑን አላወቀም። ግን ወደ ቁም ነገሩ
ለመመለስ፣ ሐጐስ ዕውቀት ዕሚን ይዘተሳል ብሎ አመ
ኑም አሳመኑም፣ "አልጀርያ ያሉት ልጆች" ብሎ ጻ
ፈው "ስድብ" በአንባቢ ዘንድ ውዜት ያስከትላል ብሎ
በማመን እንደሆነ ገልጿ ነው። ይህ የፊውዳል አስተ
ሳሰብ ነው። የኢትዮጵያን የተጠበጠ ሁኔታ አጥንቶ
ለኢትዮጵያ ረቮሉሽን ትክክለኛውን ቲዎሪ ሊያወጣ የሚ
ችለው እንደ "የልጅ ዐዋቂ" (በተለመደው አነጋገር)
ሊሆን ይችላል።

ሐ) በሰዎች መካከል፣ በተለይም በሚቀራረቡ ወዳጆች ጓዶች
መካከል መኖር በሚገባው ግንኙነት የፊውዳሉ ርዕዮተ
ዓለም ያለው አስተሳሰብ እውነተኛ መተማመንና መረቀ
ርን ባይሆን የውጭ ሰው (ቢያ) የሚያየው የመተማመንና
የመረቀር ምልክት ማሳየትን የበለጠ ዐጋ (virtue)
አድርጎ ይመለከታል። ዋናው ቁም ነገሩ ሁለት ሰዎች



መተማመናቸውና መረቀረቸው ባይሆን የውጭ ሰው "ይፈቀ
ራሉ" "ይተማመናሉ" ማለቱ ነው። ስለዚህ አንድ
ሰው "ጓደኛዬ" የሚለውን ሰው ይቅርታ የማያደርግለት
ጥፋት አጥፍተሃል የሚለው "በሰው ፊት" "በደባባይ"
የወቀሰውና ጥፋቱን የገለጸ እንደሆነ ነው። "በደባባይ
አጋለጠኝ" ካለ፣ ተቆራረጡ ማለት ነው። አንድ ጓደ
ኛን አለአገባብ እንኳን ቢሆን ለብቻው መውቀስ እንደ
ትልቅ ጥፋት አይቆጠርም። "በሰው ፊት" ግን በጥ
ፋቱ እንኳ መውቀስ፣ በተለይ የተበደለ ሰው ካለና እዚ
ያው ከተገኘ የመጨረሻ መቆራረጥን ያስከትላል፤ "ምንበ
ባጠፋ እንዴት በሰው ፊት ያጋልጠኛል" ይላል። ስለ
ዚህ አንዱ ሰው፣ በዓይና ተበዓይ፣ ገፈኛና ገፍ የተሠ
ራበት፣ በቀራኔ በተፈጠሙበት ጊዜ ለ"ጓደኛው" ቢያ
ደላ ብዙ አይወቀስም፤ "ምን ያድርገኝ" ብሎ ይታ
ለፉል እንጂ ለሐቅና ለፍትህ ርትዕ ብሎ "ጓደኛውን"
እንዲያውም አይጠበቅም። ከዚህ የባሰው ደግሞ አንዱ
ጓደኛው ማጥፋቱን ወይም መበደሉን እውቆ በይፋ ከወቀ
ሰው ቁም ነገር ውስጥ አይገባም። እንዲህም "ጓደኞች"
ተብብለው፣ ከልብ የሚተማመኑት ጥቂቶች ናቸው። ስለ
ዚህ አንዱ ሰው ለሐቅና ለፍትህ ብሎ የማያውቀውን ሰው
ደግፎ ጓደኛውን "አይኳ" እንጂ ለግል ጥቅሙ ቢል
ቢከዳው ህብረ ሰቡን ብዙ አያስደንቀውም። እንዲያውም

በጠቀሳሳው ስለመተማመን ያለው ፍልስፍና "ሰውን ውደደው እንጂ አትመነው"፣ "ሰውን ማመን ቀብሮ ነው" በተባሉት ምሳሌዎች የሚገለጽ ነው:: ይህ አስተሳሰብ ከፍተኛ መሰቀትነትን የሚጠይቅ ረቮሉሽናዊ ትግል ለማካሄድ፣ የምስጢር ድርጅት ወይም ህገ ወጥ ረቮሉሽናዊ ፓርቲ ለመፍጠር ጥረት ሲደረግና የሳብ አደፉ መደብም የጠበቀ የመደብ መቀራረብና መተማመን እንዲያደርግ ጥረት ሲደረግ፣ መሰናክል የሚሆን አድሀሪ አስተሳሰብ ነው:: ይህን አስተሳሰብ እንዲሰፋፋ ያደረገው በኢትዮጵያ ደጋዎች ለ1000 ዓመታት ያህል የደረጀው፣ የተለየ መልኩ ጦር ወዳጅ፣ የሰላም ሁኔ የማያውቀ፣ የረጋ የተዳሰለለ የነገሥታት የዘውድ ሐረግ ( dynasty ) እንኳን የሌለው፣ ወንጀልንና ጥፋትን በተቋቋመ ህግ ያልለየ፣ ደም ጠማሽ ፊውዳሊዝም ስለደረጀና፣ ህዝቡ ምን ጊዜም ነገ የሚመጣው ገዢ ምን እንደሆነ ለማወቅ የማይችል፣ ገዢዎቹ በተለዋወጡ ቁጥር ከፋና ደግ የሚባለው ተግባር ስለሚለዋወጥ በህይወቱ አምነትን እንዲያጣና፣ እግዚአብሔርን ካልሆነ በስተቀር ሰውን እንዳያምን ስላደረገው ነው::

ይህ የፊውዳል ርዕዮተ ዓለም ከዚሁ ስርዓት በወጣነው ገራ ከገፍ ጓደኞም ህሊና ላይ የጣለው ጥላ ገና ሙሉ



በሙሉ አልለቀቀም:: አንዳንዱ ጓዶች በማንኛውም ጉዳይ ላይ በግልጽና በቀጥታ እየተወያዩ የሚስማሙበትንና የሚለያዩበትን በግልጽና ቀጥታ በሆነ ቋንቋ እየተነጋገሩ በመሄድ ፋንታ፣ በደባበይ አንድ ነን፣ ጓዶች ነን እየተባበሉ ውስጥ ለውስጥ ግን እየተማሙና እየተበጫጨቁ ለውጭ ሰው ("ጠላት" ለሚባለው) ግን "አንድ" መምሰልን ይመርጣሉ:: በተጨማሪም አንዱ ጓዱን በጽሑፍ ወይም በስብሰባ ቦታ በግልጽና በቀጥታ መውቀስ፣ ጥፋቱን መግለጽ እንደነውር ይቆጥሩታል:: በህብር፣ በውስጠ ወይራ፣ በጠማማ አነጋገር (በዲፕሎማሲ ቋንቋ) "ልክ ልኩን" መንገርን እንደመጥፎ ነገር አይቆጥሩትም:: አንዱ አደገኛ የአድሀሪ ወይም የፀረ ረቮሉሽናዊ አስተሳሰብ እንዳለው አያወቁ አስተሳሰብህ "አድሀሪ ነው፣ ለውጥ" አቋምህ "ፀረ ረቮሉሽናዊ ነው" በሰው በግልጽ ቋንቋ የጥፋቱን ከፍተኛነት መጠን ነግረው በቶሎ ነገርም በፍጥነት እንዲያስብበት በማድረግ ፋንታ ትንሽና ትልቅን ጥፋት፣ የስትራተጂና የታክቲክን ስህተቶች በማይለይ ቋንቋ እያድበሰበሱ ማለፍን ይመርጣሉ:: የጥፋቱን ልክ ያጠፋው ሰውና ሌላም ሰው ሙሉ በሙሉ ተረድቶ እንዲያርምና እንዲጠበቅ ከማድረግ ይልቅ ሰውዬው "ክብረ ተነካ" "ተቀረደኩ" ብሎ "እንዳይቀየም" የበለጠ ይጨነቃሉ::

የሚገርመው ግን በሰውዬው ላይ ሐሜትን ማውራትን በመጠረቨም የፊውዳል ከሃዲነት ( treachery ) ብቻ የሚያደርገውን ድርጊት ቢፈጽሙ እንደመጥፎ ነገር አይቆጥሩትም:: የዚህ ዓይነቱ የፊውዳል "ከአንገት በላይ" መተማመን "መሳሳይ" ( hypocrisy ) ከሥሩ በነቀል አለበት:: ረቮሉሽናውያን እየተሸነጋገሉ "እርስያ እርስያ" በመባባል ከአንገት በላይ እየተ ባበሩ ሊሰሩና ሊተማመኑ አይችሉም፤ ስለአንዳንዳቸው አስተባሰብና ጠባይ የሚሰማቸውን በሙሉ "ለነገ ሰይሉ" ከተነጋገሩ፤ ለጊዜው አለመግባባትና መቃቃር እንኳ ቢፈ ጠር ዘለቄታዊ መተማመንና ጓደኝነት ሊፈጥሩ ይችላሉ፤ ሙሉ በሙሉ ይተዋወቃሉና:: የሉንዱ ጓዶች የተማሪው ማህበር የላብ አደር ፓርቲ አይደለም እንደማይሉን ተበሩ አናደርጋለን:: ልዩነቱን እናውቃለን:: አሁን ያሉት የተማሪው ማህበር ገንባር ቀደም አባሎች በኢት ዮጵያ የሚቋቋመው የረቮሉሽናዊ ፓርቲ መሰረቶች እን ደን ባይሆኑ አባሎች ይሆናሉ ብለን ስለምናምንና የተ ማሪው ማህበ ር ዋናው ተግባር አባሎችን በርዕዮተ ዓለም ማደርጀት ስለሆነ፤ ይኸንን የዘረዘርነው፤ ካሁኑ ገንባ ር ቀደም ጓዶች እንደረቮሉሽናውያን ቢያሰቡ ራባቸውን ራሳቸውን ቢያዘጋጁ ተገቢ ስለመሰለን ብቻ ነው::



3ኛ) የፊውዳሉ ርዕዮተ ዓለም የተማሪው ህሊና ላይ በቀረ ባቸው በጣም አደሀሪና ፀረ ረቮሉሽናዊ አስተያየቶ ችና እምነቶች <u>የፖለቲካ ፍልስፍናን</u> የሚመለከተው አን ደኛው ነው:: ይህም ሁልጊዜ፤ በማንኛውም ዐቢይ የፖ ለቲካ ጉዳይ ላይ (በተለይም ገልጽ ቅራኔን በስከተለ የፖለቲካ ጉዳይ ላይ) ገልጽ አቋም አለመውሰዱና የሚደገፉትን ወገን አለማሳየት ነው:: ይህ አደሀሪ አስተሳሰብ በጠባዩ ወላዋይ ለሆነው የንኡሱ ቡርዧው መደብ ተስማሚና አመቺ ሆኖለታል:: በኛ አስተሳሰብ ይህ የፖለቲካ አቋምን ከመግለጽ መቆጠብ (ጊዜ ማየት) ለተወሰኑና በይፋ ለታወቁ የፖለቲካ መሰረተ ሐሳቦች ( principles ) ታማኝ ( committed ) አለመሆን አቋምንና እምነትን ደብቆ ትንሽ አጋጣሚ ሲገኝ የመጠረቨውንም ወረፋ ሥራ ቢሆን ሠርቶ ራስን የሚጠቅም የፖለቲካ ድርጊት መፈጸም በጠቅላላው የፊውዳ ሊዝም (በተለይ መለስ እያሉ የጠቀበው የቢዛንታይን ፖለቲካ) ጠባይ ቢሆንም በኢትዮጵያ የፊውዳል ፖለቲካ አስተሳሰብና ድርጊት ውስጥ በጣም ሰነ ብሶ ታይቷል:: ከዚህም በላይ የራሱ የተለየ መልክ ያለው የኢትዮጵያ ፊውዳሊዝም ይህ ፍልስፍና የበፊውን ህዝብ እምነት እን ዲ ሆንና የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍ ዘይቤና የህዝቡ የአነጋገር ዘይቤ መሠረት እንዲሆን አድርጓታል፤

ጠቅላላ ህብረ ሰብዊ እሴትነትም( Social value ) እንዲሆን አድርጎታል ብለን እንገምታለን:: የዚህም ምክንያት ከላይ የጠቀስነው ለ1000 ዓመታት ያህል በሚሆን ታሪኩ በደታው ኢትዮጵያ የተስፋፋው የፊውዳል ስርዓት ሰላምንና እርጋታን የማያውቅ ደም ጠማሽ ወታደራዊ ፊውዳሊዝም ስለነበረ ነው:: የፊውዳል ገዢዎች ራሳቸው መሬታቸውንና ማዕረጋቸው ሳይቀር ከወታደርነት አገልግሎት ጋር የተያያዘ፣ ሀገሪቱ ቋሚ ዋና ከተማ እንኳ ያልነበራት መሆኑን ወዘተ...ማስታወስ ይገባል:: ይህ ሰላም የማያውቅ ወታደራዊ ፊውዳሊዝም የኢትዮጵያን ህብረ ሰብ በአርበኛ ኃይሎችና በባህል ( culture ) በፍልስፍና (የፖለቲካ ፍልስፍና) በኪነ ጥበብ አስገራሚ በሆነ መጠን ወደ ኋላ የቀረ ከማድረጉም በላይ፣ ህዝቡን የሚጨቁኑትን ህጎች እንኳ ቋሚ መልክ አልሰጧቸውም ነበር:: የገዢዎች ጠባይና አመል በየጊዜው እንደተፈራረቁት ሰዎች የሚለያይ ከመሆኑ የተነሳ የፖለቲካ አቋም ወስዶ አንዱን መደገፍ ወይም መቃወም ፈጽሞ የማያስተማምን፣(ባጭር ጊዜ በወርነት) ሊለወጥ የሚችል በመሆኑና ጥሩ ትና ደግነት፣ ህገና ወንጀል አለመለየቱ የሚያስቀጡና የማያስቀጡ ህገና አስተሳሰብ እንኳን ለማወቅ የማይመች በመሆኑ ማንኛውንም የፖለቲካ አስተሳሰብ በግልጽ መግለጽ



አደገኛ ሆኖ መገኘቱ አልቀረም:: ስለዚህ ያለው መንገድ ሁለት ትርጉም ባለው በሚያሻማ (በነዓፍታ የሚያማገስና የሚሰደብ፣ የሚወቀስና የሚያስመሰግን) አነጋገር (ህብር፣ ሰምና ወርቅ፣ ምሳሌያዊ አነጋገር ውስጡ ወይራ፣ ምፀት፣ አሽሙር ...ወዘተ) አፅፀፍ መግለጽ ብቻ ነው:: እርገጥ፣ ይህ በጠቅላይ " AESOPIAN " ቋንቋ ተብሎ የሁሉም ብሮች ቋንቋ ቢሆንም በኢትዮጵያ በተለይ በአማርኛ ቋንቋ (ማለት በጣም የደረጀው የፊውዳል መደብ ቋንቋ) ቋሚ የስነ ጽሑፍና የአነጋገር ስልትና ዘይቤ ሆኖአል:: ስለዚህ በማንኛውም አደጋ በሚያስከትል ቀራኒ በአለበት ጉዳይ ላይ (በተለይ በፖለቲካ) አቋምን በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ ገልጾ ከሚቀጋው ይልቅ በ'ዘዴ' 'በታክቲክ' ከሁለቱም አለሁ ብሎ የሚያመልጠው ሰው ይሞገሣል፤ 'እሱ አቦ አይያዝም 'ይባላል:: ስለሆነም አቋሙን ከመጀመሪያው ገልጽ አድርጎ ወገኑን ከሚለው ሰው ይልቅ አቋም ባይወስድ ቀርቶ፣ ጊዜ ጠብቆ፣ "የሚያቀጣውን" ወገን የሚደግፈው "ብልህ" " ዐዋቂ"፣ ይባላል:: ባጭሩ አቋምን ቶሎ መግለጽ "ችኩልነት" ይባላል፤ በቁጣና በንዴት በስሜትም መናገር ገፊኞችንና ቀጣሪያችን እንኳን፣ መስደብ " ቅሌት" ይባላል:: በጠቅላላው በአነጋገር አስተያየቱን ገራቀኝ ባይል፣ ድርቅ ባለ ቁርጥ አነጋገር ከሚገልጸው፣ ሰፋፍኖ ግንንም(አጥፊና በዓይነ ጭምር) በማስቀየም ቋንቋ ወይም ሁለቱም ወገን "ደገፍናል"

በሚሉበት ሁኔታ የሚናገረው ይሞገሳል፣ 'አንደበተኛ'
ይባላል::

ይህ ርዕዮተ ዓለም በግራ ክንፍ አስተሳሰብ ላይ ባይ
ቀር ተቀርጿል:: አንዱ ሰው የሚሰማውን በግልጽ ቋንቋ
ከሚገልጽ ይልቅ፣ ፊደል እየቆጠረ፣ ድምፁን ዝቅ አድ
ርጎ ቢናገር የተናገረው ዕውነተኛ አቋሙን ባይገልጽ
እንኳ ይሞገሳል:: ጓደኛውን በግልጽ ቋንቋ ከሚወቅ
ሰው፣ ጓደኛውን ቢበድብ ቀስ እያለ ወጋ የሚያደርገው
ይበቀለታል እንጂ አይወቀስበትም:: የፖለቲካ አቋም
በመሠሰዱም በኩል እንዲሁ ነው:: አቋሙን ከመጀመሪያው
ገልጾ አውርቶ ተናግሮ የሚመጣውን አደጋና ወቀሳ ለመቋ
ቋም ከሚዘጋጀው ይልቅ፣ ፀጥ ብሎ ከርሞ አብዛኛው የሚ
ያስበውን ተመልክቶ ወይም አደጋ የሌለበትን አቋም ደግፎ
ትልቅ 'አቀቂ' በመምሰል በመጀመሪያው አቋም ቢወበት
አገረ መንገዶቻውን ትንሽ እንኳን የተገኘባቸውን በመዝ
ለና የሚመፀደቀውን ሰው አዳማጩ እንዳሳወቀ ክም ብሎ
ያልፈዋል:: ይህ የረቮሉሽናዊያን መንገድ አይደለም::
የፖለቲካ አቋምን *በማንኛውም ጊዜ በሁሉም ጉዳይ ላይ*
በተለይም ጉዳዩ አከራካሪና አደገኛ በሆነበት ጊዜ የሚ
ገልጽ ቀጣፊ፣ አጭበርባሪና የፊውዳል ፖለቲከኛ ነው::
አደጋ የሌለበትን ተመልክቶ ነፋስ የሚነፍስበትን አቅ
ጣጫ አይቶ፣ አቋም የሚወስደውን ቢሊ ማን አምኖት



አብሮት ይሰራል፣ እዚህ ላይ አንዲት ጥቅስመጥ
ቀስ እንፈልጋለን::

" All party Comrades, and it goes without saying for senior party cadres, must be *frank* and *forthright* politically. At *all times* one ought to state one's political views *openly* and on *every* important political issue, *express ones position*, either for or against, adhering to what is right and correcting what is wrong."( Peking Review, December 10, 1971 – ያሰመርነበት እኛ ነን)

ይህንን ከጠቀስን ፓርቲና የተማሪ ማህበርን አማታ
ችሁ እንደማንበል ተስፋ አለን

ለመደምደም ያህል የምንጠቅሰው የሚከተለውን ነው::
የተማሪዎች ማህበሮችን የግራ ክንፉ ባይቀር፣ በፊው
ዳል ርዕዮተ ዓለም ሙሉ በሙሉ ያልነፁ ናቸው::
ተማሪው የኢትዮጵያ ህዝቦች ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢም
ፔርያሊስት ይሁኑ እያለ ሲለፍፍ ራሱ የሚቆስረቢያዊ
መንፈስ በሚገባ ያልተቀሃደው ሆኖ ይገኛል:: በግራ
ክንፉ ውስጥ አባሩሪ የፊውዳል የፖለቲካ የትግል ዘዴ

ይገኛሉ:: ማህበሮቻችን ዲሞክራሲያዊ ካልሆኑ ሊያደርጉ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ዕውነተኛ ነጻነት ደህንነት የሚያጎ ሰዎችን ለማፍራት አይችሉም:: ሶሻሊዝም የሚመሠረተው በዲሞክራሲ ላይ ነው:: ማርክሲስት ሌኒኒስት ነኝ በማለት ዲሞክራሲ ለቡርዧ መደብ ጥቅም ብቻ የሚውል የፖለቲካ ስርዓት በማስመሰል የዲሞክራሲን አስተሳሰብ፣ መንፈስና መሠረተ ሀሳቦች የሚያናንቅ ጥራዝ ነጠቅ፣ ፊውዳሊዝም የሚወድቅበትን መንገድ የማያውቅና ፊውዳሊዝምን የሚደመስሱት ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ናቸው ሲባል በርዕዮተ ዓለማቸው የዲሞክራሲ አስተሳሰብ የተቀረፀባቸው መደቦችና ዲሞክራሲን ተግባር ላይ የሚያውሉ የላብ አደሩ ፓርቲ መሆናቸውን የማያውቅ ነው:: አንዱ ሰው የማርክስን፣የሌኒንን ወይም የማኦን ጽሑፎች አንብቦ ለመጠቃቀስ ስለቻለ የላብ አደር ወገን ሆነ ወይም የላብ አደሩ ርዕዮተ ዓለም ተቀብሏል ለማለት አይቻልም:: አንዳንዱ የሀርቫርድ፣ የኦክስፎርድ ወዘተ ቡርዧ ፕሮፌሰሮች እነዚህን ታላላቅ የላብ አደር መሪዎች ምናልባትም ከአብዛኛው የሠራተኛ መደብ ፓርቲ አባሎች የበለጠ አንብበዋቸዋል፣ የበለጠ ሊጠቃቅሷቸው ይችላሉ ነገር ግን ይህ የመጽሐፍ ዕውቀታቸው የነዚህ የላብ አደሩ



መደብ ፓርቲ መሪዎች ሐሳብ ተከታዮች ሊያደርጋቸው አልቻለም:: በኢትዮጵያ ተማሪዎች ዘንድ የማርክስን፣ ሌኒንንና የማኦን መጽሐፍት መጥቀስ፣ የነሱን ሀሳብ አደገፋለሁ ማለት እንደ "ፋሽን" ተወስዷል:: ምክንያቱም ዛሬ እንዲህ ማለቱ አደጋ የለበትም:: ጉዱ የሚፈላው በማርክስ፣ በሌኒንና በማኦ ቲዎሪ መሠረት፣ የኢትዮጵያን ሁኔታ ተንትናችሁ አቅርቡ፣ ቲዎሪዎችን በተግባር ላይ አውሉ ሲባል ነው:: አሁን በአገራችን አደጋ የሚያስከትለው ምስጢራዊ ረቮሉሽነሪ ድርጅት አቋቁሞ ዕውነተኛ ረቮሉሽናዊ ተግባር ማካሄድ ነው:: ሌላው ትንሽ አደጋ ያለበት ነገር ህዝቡ ሊያውቀው በሚችል ሁኔታ መንግሥቱን በስትገፋት የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ አቋም ወስዶ ፕሮፓጋንዳ ማስፋፋት ነው:: ከነዚህ ጉዳዮች ቀናው የብሔሮች ጉዳይ ነው:: ስለዚህ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት አባሎች በተለይም የመሪነት ኃላፊነት የተሸከሙት ጓዶች ያለባቸውን ኃላፊነት ተረድተው በኢትዮጵያ ህዝብና ተራ ተፖለቲካ ሁኔታ ምክንያት የተማሪዎች ማህበራት ያለባቸውን ልዩ ታሪካዊ ኃላፊነት ተረድተው ረቮሉሽናዊ ድርጅትን ከዚያም ረቮሉሽኑን ሊያገለግሉ የሚችሉ ዕውነተኛ ዲሞክራሲያዊ መንፈስ የተዋሃዳቸው፣ ከፊውዳልና ከሌላም የጨቋኝ ስርዓት ርዕዮተ ዓለም የነፁ ጓዶችን የሚያስለጥኑበት መንገድ እንዲፈልጉ እናሳስባለን::

በመጠረሻም መልክታችንን የጻፍነው በንፅህና በቅን
መንፈስ፣ በልብ የተሰማንን ልክ እንደተሰማን ስን
ሸፋፍነን ነውና ጉብኢውና ተጋቀስን ብለው የሚያምኑ
ጊዶች መልእክታችንን በቅን መንፈስና በረቮሉሽናዊ
ድፍረት እንዲቀበሉልን እንጠይቃለን:: ሂስ ብቀረ
በንብቻው ጉዳዮች ላይ የተለየ አስተያየት ያላቸው
ሰዎች ካሉ በጻፍነው ጽሑፍ ወይም በሌላ ዝሁ በይፋ
በገለጽነው ወይም በሰማችን በወጣነው ጽሑፍ ላይ
የተመሰረተ፣ በገልጽ ቋንቋና በይፋ የሚቀርብ ሂስ
እንጂ "አውነተኛ ባሳማቸው" "እነሱ የሚፈልጉት"
"እነሱ የሚሉት" እየተባለ በሰላዮችና በአድሀሪያን
በሚነዛበን ወሬ ላይ የተመሰረተ አሸሙርና ውስጠ
ወይራ የተሞላበት ዘለፋ እንዳይሰነዝሩብን አደራ እን
ላለን:: እስተሳሰባችንን በመሰላቸው ተርጉመው ሰዎች
ለሚሰጡን ፖለቲካዊ ስያሜ ፔቲ ቡርዧ ናሽናሊስት፣
አናርኪስት፣ ሶሻል ሾቪኒስት ወዘተ ፡ ኮ ግዱ የለንም፤
ያበረታታናል፣ የተባበቀ መሆናችንን እናስረዳለን ወይንም
ራባችንን እንለውጣለን:: በሰላይና በአድሀሪያን ፕሮፖ
ጋንዳ ተገፋፍተው "ጊዶች" ለሚሰነዝሩብን ተንኮል፣ የፊ
ውዳል አሸሙርና ውስጠ ወይራ ላለበት "ሂስ" ጠርቦ ትዕ
ግስት የለንም፤ ይዘገንነናል፤ ገን ምን እናደርጋለን፤
ሥራቸው አስኪያጋልጣቸው እንጠብቃለን::

የኢትዮጵያ ተማሪያች ዲሞክራሲያዊ ረቮሉሽነሪ አንድነት